**16 ነሐሴ 2008 አ/ም**

## የናዚ እልቂት በወልቃይት ጠገዴ (በበጌምድር) ህዝብ ላይ በወያኔ ሲደገም ምን ይመስላል?

በ25 አመታት ውስጥ በተለያዩ የኢትዮጵያ አከባቢ ጥቂት የሚባሉ መልካም ለውጦች ቢኖሩም እንኳ ጀግናው የኢትዮጵያ ዳር ድንበር አስከባሪው መስዋእት ከፋዩ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ አይደለም የመልካሙን ለውጥ ሊያጣጥም እንዲያውም በተቀነባበረ ሁኔታ የዛሬ 41 አመት ከነበረበት የህልውናና ኑሮ ብዙ እጥፍ አሽቆልቁሎ ተምዘግዝጎ ወርዶበታል፤ ወያኔ አሰቃይቶታል፤ ህይወቱና አኗኗሩ አመሰቃቅሎበታል፤ ለብዙ መከራና ስቃይ ሞትና እንግልት መታሰርና ደብዛ መጥፋት መሰደድና መሸማቀቅ ዳርጎታል። የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በተለይ ሁኔታ ደግሞ ከ1972 አ/ም ጀምሮ የወያኔ ፋሽሽታዊ መርዝ በላዩ ላይ የተርከፈከፈበት ህዝብ ነው። አሳዛኙ ነገር ወያኔ የፈጠረው ችግር በሁሉም የኢትዮጵያ መርዙን ከመትፋቱ ጋር ተያይዞ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወገኑ የየራሱን ህመም ሲያዳምጥ ስለኖረ ከህመም ሁሉ ህመም፣ ከስቃይ ሁሉ ስቃይ፤ ከእልቂት ሁሉ እልቂት ሲፈጸምበት፣ በእስራኤላውያን ላይ በኦሽዊትስ ካምፕ በናዚዎች የተቀነባበረው የዘር ማጥፋት በ21ኛው መ.ክ.ዘ በወያኔዎቹ የአፍሪካ የነፃነት አርማ በሆነችው አገራችን ኢትዮጵያ በከፋ ሁኔታ በግልጽና በድብቅ ሲደገም ምንም አይነት የሚዲያ ሽፋን ስለማይደርሰው ኢትዮጵያዉያን ወገኖቹ ሊያውቁለትና ሃይ ሊሉት አልቻሉም መከራዉን በተለይ ደግሞ ከ1972 አ/ም ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ሳይደርሱለት ብቻውን ሲጎነጭ ኖሯል።

እዚህ ላይ ለማሳሰብ እምፈልገው ዋና ነጥብ የወልቃይት ጠገዴ አማሮች በአማራነታችን ምክንያት ብቻ ካሁን በፊት የደረሰብንና አሁንም እየደረሰብን ያለው የዘር ማጥፋት ዘመቻና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ረገጣ አረመኔ ህወሃት *'በመልካም አስተዳደር* 'ስም ለማስተባበል መሞከር በፍጹም አይቻለውም፤ የመልካም አስተዳደር ችግርማ በተለያየ መጠንም ቢሆን በአለም ዙሪያ ይኖር ይሆናል። መልካም አስተዳደር የሚባለው የህወሃት ቋንቋ ወያኔ ካሁን በፊት የፈፀመውንና አሁንም እየቀጠለ ያለው አረመኔያዊ ጭፍጨፋና የሙብት ረገጣ ህጋዊ አድርጎ ለማስቀጠልና ዘራችን ፈፅሞ እንዲጠፋ በማሰብ የተሴራ

ፋሽሽታዊ ቋንቋ ነው። አንድም የለመዱትን የመስፋፋትና ከዛም የመገንጠልና ኢትዮጵያን የማፈረካከስ አላማ በውስጡ ያቀፈ ሰይጣናዊ አላማ ነው።

ወገናችን የሆነው የተከበረው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊይዝልንና ሊረዳልን የሚገባው ነጥብ  የእኛ ዋናው (የወልቃይት ጠገዴ አማራ ህዝብ) ጥያቄ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ሳይሆን የወልቃይት ጠገዴ ህዝብና መሬት አማራ ስለሆን ወደ እናት አገራችን ወደ ጎንደር ወደ አማራነታችን መልሱን የሚል ነው። ሰላምን ፈልገው ከመለሱን እጅግ ደስ ይለናል ካልሆነ ደግሞ የእነርሱ ፈቃድና ምስክርነት ሳያስፈልገን በራሳችን ራሳችንን አማራነታችንን አስረግጠን እንመልሳለን።በቃ ይሔው ነው!!! ይህ በትግራይ ተስፋፊና ነጻ አውጭ ቡድን፣ በትግራይ ፖሊስ፣ በትግራይ ልዩ ሃይል፣ በአጋዚ ወታደር፣ በትግራይ አስተዳደር አመራሮችና ካድሬዎች ማዳፈን የማይቻል የሚፋጅ ረመጥ ጥያቄ ነው።

የኢትዮጵያ ወገኖቻችን ሆይ አንድ ሚሊየም (1, 000 አመት) ሙሉ ያለው ታሪክ የሚመሰክረሰው እውነት የወልቃይት ጠገዴ ህዝብና መሬት የአማራ እንጂ የትግሬ ሆኖ እንደማያውቅ ቁልጭ አድርጎ የሚያስረዳ መሆኑን ነው። የታሪክ  መዛግብት ከሚመሰክሩት እውነት በተቃራኒ ታሪኩን በማዛባት እንደማጣቀሻ ከሚያቀርቡ የትግራይን ህዝብ ይወክላሉ ብለን በማናምናቸው  የወያኔ ባንዳ የሆኑ የታሪክ ሙሁር ነን ባዮች ፋሽስት ለምሳሌ እንደ  ዶ/ር  ገላውዲዮስ ያሉ የውሸት ታሪክ አጣቃሾች በእውነት ታሪክና ህግ እንደሚፋረዳቸው እናምናለን። በነገራችን ላይ ገላውዲዮስ በትግሬኛ የአሜሪካን ድምጽ ሬድዮ ቃለ ምልልስ ሲያደርጉ ያጣቀሱት መጽሐፍ መጽሐፉ ከሚለው በተቃራኒ ስለሆነ ክስ ለመመስረት ዲግሪያቸውን ለማስነጠቅና ሌላም ህጋዊ ቅጣት እንዲወሰድባቸው ሙሁራኖች እየሰሩ ነው። በዉሸት ለሆዳቸውና  ከዛም በላይ ብለው ህሊናቸውን ያቆሸሹ ቀኝ እጅ ሆነው የወያኔን ገፅታ በመገንባትና ተመሳሳይ ፋሽሽታዊ አላማን የሚያሳኩ ከፋሽስት ወያኔ ጋር ሴት ተቀን በመስራት የህዝብን ጥያቄ አዳፍኖ "<u>አስመሳይ የህግ ካባ</u>" በማልበስ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ብሎም የመላ አማራውን ዘር ለማስጨረስና ካሁን በፊትም ለተፈፀመው እልቂት ከተጠያቂነት ለማስመለጥ የሚሯሯጡ ቀንደኛ ጠላቶች ላይ

የኢትዮጵያም ሙሁራን በአለም ህግ ፊት እንዲያቆሙልን በትህትና እንጠይቃለን። አዎ የኢትዮጵያ ሙሁራን ወገኖቻችን ሁላችሁም ይሄንን የአስመሳይነት የወንጀል የወያኔ ጭምብል አውልቃችሁ ው አያኔን ባዶ በማስቀረት በአለማቀፍ የጦር ወንጀል ፍርድ ቤት ባስቸኳይ ይቀርቡ ዘንድ እርዱን። መማራችሁ የወገናችሁን ህልውና ለማስቀጠል ካልረዳ እናንተንም ሰላም አይሰጣችሁምና፤ ከእራሳች ጋር ያጣላችሏላና።ይሄን የጨለማ ዘመን አልፈን ዘራችን መቀጠል ከቻለ ይህ መደረጉ ለመጪው የ አማራና የትግሬ ህዝብ ሰላም ወሳኝነት ይኖሮዋል ብለን እናስባለን።  ሌላው የተማረ ኢትዮጵያዊ  ያለ የማይመስላቸው ጠባቦቹና ዘረኞቹ የትግራይን ምስኪን ህዝብ የማይወክሉ ገንዘብ አምልካቸው የሆነባቸው ህሊናቢስ ወረበሎች የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ አግሞ ሙሁሩ በቃችሁ ሊላቸው ይገባል። በዚህ አጋጣሚ የታሪክ እውነተኛ ሙሁሩ ወጣት አቻምየለህ ታምሩን ሙሁራዊ በሆነ መንገድ ስለሚያደርጉት የውሸተኞች ካድሬ ሙሁሮችን ሴራ  ባዶ የማድረግና  የመርታት ጀግንነት የሚደነቅ ከመሆኑም ባሻገር ለእውነት መቆም ነውና በወልቃይት ጠገዴ  ህዝብ  ስም እንዲሁም በመላ የአማራ ህዝብ ስም እጅጉ ልባዊ ምስጋና እንዳስተላልፍላቸው ይፈቀድልኝ። እንዲሁም <u>ሁሉም ክቡራንና ክቡራት የቤተ-አማራ ውድ ልጆች</u>፣ ክቡር አቶ ተክሌ ይሻው፣ክቡር አቶ አማረ አፈለ፣ ክቡር ወጣት ሙሉቀን ተስፋው፣ ክቡር ልኡል ራስ መንገሻ ስዩም፣ ክቡር አቶ ገብረመድህን አርአያ፣ ክቡር አቶ ያሬድ ጥበቡንና ሌሎች ውድ  የኢትዮጵያ አንድነት የሚገዳቸውና አጥብቀው የሚሰሩ እውነተኛ  ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ  አብዛኛው  ሙሁር በወልቃይት ጠገዴ ዝምታውን መርጦ  የወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ህዝብ እንደበግ ለመታረድ ወያኔ የውሸት ታሪክን እንደቅመም እየተጠቀመበት ባለበት ስአት እውነተኛ ቃላቸውን ስለሰጡ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ልዩ ምስጋናየን አቀርባለሁ። ሌሎች ሙሁራን ተሳትፎ እንዲያደርጉ አሁንም ህዝቡ የድረሱልኝ ጥሪውን በማስተጋባት ላይ ነውና እባካችሁ ድረሱልን!!! ተሳትፎ ያደርጋችሁ ሙሁራንም  ሳትለዩን የአገራችን ህግ በወያኔ ምክንያት ካልዳኘን ወደ አለማቀፍ ህግ ጉዳያችን ወስዳችሁ ከሞት እንድትታደጉን እርዳታችሁ እንዳይለየን በእግዚአብሔር ስም አደራ እንላለን።

ወያኔ በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ይህ ሁሉ ስቃይ የሚፈጸምበት ምክንያት በዋነኝነት ህዝቡ ፍጹም በኢትዮጵያዊነት የሚያምንና የሚያስቀድም ከዘረኝነት የጸዳ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ህዝብ ስለሆነ ነው። ይህ የህዝቡ የስንት ሺ አመታት አኗኗርና አካሄድ ከወያኔ የከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ስለሆነ በቀጥታ የወያኔ እርምጃ ሰለባ እንዲሆን አድርጎናል ብለን እናምናለን። በሌላ አነጋገር በኢትዮጵያዊነት እምነታችን ዘር ሳንቆጥር መኖራችን ሰለባ እንድንሆን አደረገን ማለት ነው።ወልቃይት ጠገዴና ጠለምት እስከቅርቡ ድረስ በኢትዮጵያ የሚገኙ የተለያየ ብሔር ያላቸውን ውድ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ከዛም ባለፈ ለአፍሪካዉያንም ጭምር በዋነኝነት ደግሞ ሰሜንም ደቡብም ሱዳናዉያን የመሳሰሉ የአፍሪካ ዜጎችም ሰርተው ህይወታቸውን ቀይረውበት በሰላምና በፍቅር ደስ ብሏቸው የሚኖሩበት ህዝባችን ከኢትዮጵያዊነቱ በዘለለ በአፍሪካዊነቱም የማይታማ በጣም ለምና በተፈጥሮ ሃብት በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም የሆነ አካባቢ በመሆኑ ዘረኞቹ ወያኔዎችና አሽቃባጭ ጥቅመኛ ተከታዮቹ ትግሬዎች የተፈጥሮ ሃብቱን ቋመጡት፤ ኢትዮጵያዊ ስሜቱንም አልወደዱትም። ህዝባችን ባለው ኢትዮጵያዊ በጋራ ተካፍሎ የመኖርንና የመቻቻል ባህላችን ወደጎን ብለው፣ ማንነታችን በመንጠቅ አዲስ የትግሬ ማንነት በላያችን ላይ ጭነው ጭራሽ አይናቸውን በጨው አጥበው ይህ መሬት ቅድሚያ ለትግሬ ብለው እኛን በልዩ ልዩ መከራ ማሰቃየት ጀመሩ። ህዝባችንን አጥፍተው '<u>ታላቂቷን ትግራይ</u>' ን በመመስረት ከሱዳንና ኤርትራ ጋር እንዋሰናለን አማራም እናጠፋለን ብለው ተነሱ። የሚገርመው ነገር ላለፉት 36 አመታት እነርሱ የሚፈጸሙት ስቃይ አላረካ አልበቃ ብሏቸው በሱዳን ልዩ ሃይሎች ከፍተኛ የአፈናና ግድያ አስፈጸሙበት። የስንቱ የአገር ጀግናና የአገር አልኝታ ህይወት ቀጠፉት አስቀጠፉት መስላችሁ! ጀግናው ህዝብም የሚቻለውን ያህል ታገለ ቢሆንም ግን ወያኔ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ ብኋላ ወታደራዊ ሃይሉን አጠናክሮ በመምጣት ቦታውን ተቆጣጠረ ህዝቡንም በተለይም ወንዶችን ልክ እንደፈርዖን እያደነ ማሰር፣ ማሳደድ፣ ማሰቃየትና መዝረፍ ጀመረ በተለይ ከ1983 አ/ም ጀምሮ።

የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ይህ ሁሉ ግፍ፣ መከራና እልቂት ሲጎነጭ፤ ህዝብ እንደህዝብ በመስቀል ሲሰቀል ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹም አላወቁለትም። ኢትዮጵያን ለማፈራረስ በተነሳው ገንጣይ የወያኔ ቡድንና ግብረ-አበሮቹ ህጻን አዋቂ፣ ወንድ ሴት፣ ገበሬ ነጋዴ፣ቀይ ጥቁር፣ አጭር ረዥም፣ ገጠር ከተማ፣ ሃብታም ድሃ ፣ ያገባ ያላገባ፣ ቆላ ደጋ ሳይለይ ሌት ተቀን ለ36 አመታት በተቀነባበረና ሳይንሳዊ አካሄድ በተሞላበት መንገድ ሞት፣ ስቃይና እንግለት ተፈጽሞበታል፤ ንብረቱ በቀጥታ በወያኔ ተዘርፏል፤ በእጅ አዙርም በሱዳኖች አሠርፏል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን አሁንም ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ አላወቁለትም፤ ከህመም ሁሉ ህመም ይሉሃል እንዲህ ነው!! እንዲያውም ከዚህ በተቃረነ መልኩ *"የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ትግሬ አይደለም እንዴ ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ የሚያደርሰው ስቃይ በሌሎች ብሔር ብቻ አይደለም በእኛ በትግሪዎቹ ላይም ይፈጸመዋል ለማለት ፈልጋቹህ ነው?"* የሚሉ አንዳንድ ሁኔታውና መሰረታዊ ችግሩ ያልገባቸው ወገኖችም አልጠፉም። በወያኔ የፖለቲካ ሴራ ተጠልፎ መውደቅ ማለት ይሔ ነው። እውነታው ግን ፍጹም እንደዛ አይደለም፤ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ጠለምትም ጨምሮ ትግሬ ሳይሆኑ አማራ ናቸው። ይህ ሁሉ ግፍና የዘር እልቂት የሚፈጸምበት ስለ ሁለት አበይት ምክንያት ነው። እነርሱም፦

1ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ የበጌምድር የጎንደር አማራ ህዝብ እንጂ ወያኔና ካድሬዎቹ እንደሚሉት ትግሬ ባለመሆኑ ነው፤ ለዚህም ስለ እውነት ይመስከር ቢባል ወያኔና ካድሬዎቹ ጥሩ ምስክር ይሆኑ ነበር። ትግሬም እንዳልሆነ ስለሚያውቁም ነው ይህ ሁሉ የእልቂት ግፍ ለ36 አመት የፈጸሙበታና አሁንም እየፈጸሙበት ያሉት። ሌላኛው ነጥብ ደግሞ ህዝቡ ትግሬ ቢሆን ኖሮ ትግሬነት በራሱ ጥቅም በሚያሰጥበት ወቅት ለምን ታድያ እውነትኛ የትግሬ ማንነቱን ጥሎ አማራነትን ይመርጣል? ለዛውም አማራነት ማለት "ወንጀል" አማራነት ማለት "ሞት፣ ስደትና መፈናቀል" ማለት በሆነበት ስአት? እስቲ አስቡት በአንጻሩ ደግሞ ትግሬነት ትግሬነት ማለት "ሃብታምነት፣ምርጥ ዘር፣ የበላይ ገዥ፣ ባለስልጣን" ማለት ሆኖ የተለያየ ጥቅም በሚያስገኝበት ስአት "አንድ ህዝብ አማራ ነኝ!..ትግሬ አይደለሁም" ብሎ እንዴት ይነሳል? ይሔን ጥያቄ አንድ ደረጃ ከፍ እናድርገውና በኢትዮጵያ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ

እንዲህ በሆነበት ግዜ ጭራሽ እነርሱ እንደሚሉት እንዴት ትግሬ ሆኖ ሳለ አማራ ነኝ ይላል? ወያኔ እንደሚለው የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝብ ትግሬ ቢሆን ኖሮ በቁጥር አናሳ ህዝብ ነን ብሎ የሚጨነቀው ወያኔ እንዴት ይህ ሁሉ ጭፍጨፋ "ትግሬዎች በሆኑ ወግኖቹ" ሊያጧጥፍ ተነሳሳ? አያችሁ ወያኔ በጣም ወንበዴና ህሊና-ቢስ ነው። የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ህዝባችን "መሰረታዊ የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው" ተብሎ በወያኔ የተፈረጀ ንጹህ አማራ እንጂ ትግሬ አለመሆኑ አመክዮያዊ ተዋረዱ በራሱ ወደ እውነት መንደር መርቶ እውነትን ቁልጭ አድርጎ ይሳስየናል። ህዝባችን ትግሬ ባለመሆኑ ምክንያት ነው "እኔ ትግሬ ሳልሆን አማራ ነኝ" ያለው። ይህን ህጋዊ የህዝቡ ጥያቄ በማዳፈን ማለፍ አይቻልም አሁን ማለት ትላንት ማለት ስላልሆነ!!! የትላንቱ ፋሽሽታዊ አካሄድ ካሁን ብኋላ ሊገታ ይገባዋልና፤ የተበደለም ሙብቱ ተከብሮለት ሊካስ ግድ ይለዋልና። ሳይሆን ቢቀር ግን በዳዩ ሊቀበር ፅዋው ሞልቶ የፈሰሰ የሚወራረድ የግፍ ግድ አለበትና!!! መተላለቁም ከትውልድ ትውልድ የሚቀጥል ተቀጣጣይ እልቂትን የሚጋብዝ የሞት ሃወልት የሚትክል የእብሪተኛ ወያኔ የጥሪ መታሰቢያ ነውና። የሚደንቀው ባለፈው መጋቢት ሁለተኛው ሳምንት 14ና 15 ላይ በሁመራ <u>አባይ ወልዱና አባዲ ዘሞ</u> ካድሬዎች ሰበሰበው *ይህ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ የማንነት ጥያቄ ለማዳፈን 80 ሚሊዮን ብር ወጭ እንዳደረጉና ይህም እስካሁን ድረስ ማስቆም ስላልተቻለ እርምጃ እንደሚወስዱ* በድጋሚ በድፍረት ተናገሩ። ተወላጆቹ ካድሬዎቹ ግን ይህን አንመክርም የለንበትም በማለት በድፍረት እዛው ስብሰባው ላይ እቅጩን ነገሯቸው። ህዝብ ለማጫረስ የሚደረግ የድንቁርና ውሳኔ ካልሆነ በቀር የወልቃይት ጠገዴ የአማራ ማንነት ጥያቄ በፍጹም ማስቆም እንደማይችሉ ሊያውቁት ይገባል። እኛ በአሁኑ ስአት ለሞት የሚፈራበት ምንም አይነት ምክንያት የለውም... መፍራት ካለባቸው በድሎት ያሉት እነርሱ ናቸው፤ እኛማ ለየትኛው ህይወትና ኑሮ ብለን ሞትን እንፍራ? የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያውቀው የተገባ ነገር ቢኖር ካሁን ብኋላ በከፍተኛ ሁኔታ የትግራይን ህዝብ በሰፊው በየጥጋጥጉ በስውር እየቀሰቀሱ እልቂትን እየተጣሩ ስለሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚመጣው የርስበርስ ጦርነት ተጠያቂዎቹ ወያኔና ወሮበላና እብሪተኛ ተከታዮቹ የትግራይ ተወላጆች ተጠያቂ ናቸው። አዎ ወያኔ በከፍተኛ ሁኔታ የትግራይን ህዝብ እየቀሰቀሰ ነው ያለው፤ እንግዲህ ማን ሞቶ

ማን በህይወት መኖር እንደሚችል አብረን ለወደፊቱ የምናየው ነገር ነው የሚሆነው። የዛን ግዜ ሰው ይበለን።

2ኛ. አንድ ካድሬ በ1984 አ/ም እንደተናገረው ለታላቂቷ ትግራይ እጅ መንሻ "የወልቃይት ጠገዴ መሬቱና ሴቱ ስለሚፈለግ" ብቻ ነው። ይህም በድብቅ ሳይሆን በየስብሰባ መድረኮች ተናግረው በተግባር ሲፈጸም አይተናል።

በዚህ ጽሑፍ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ከደረሱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ግፎች መካከል ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለግንዛቤ ያህል ጥቂቶቹን እጠቅስላችኋለሁ። ይህም ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ያለንበት አጣብቂኝ ሁኔታ ተረድተው ጨርሰው ሳያጠፉን እንዲደርሱልን ለማሳሰብ ነው እንጂ በሌላ ግዜ ለአለማቀፍ ማህበረሰብ የሚሆን ጽሑፍ በሰፊው አዘጋጅቼ እመለስበታለሁ። አሁን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ወያኔ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ሙሉ የዘር ማጥፋት እቅዳቸውን እንዴት ሲያከናውኑ እንደቆዩና አሁንም አይከናወኑ እንዳሉ ከዚህ ጽሑፍ ተነስታችሁ መተንበይ አያቅታችሁም። አሁን ግዜ ሳልወስድባችሁ ወደ ነጥቦቹ ላሸጋግራችሁ። ከዚያ በፊት ግን መላው የ አማራ ህዝብ ለወገኖቹ ሲል ለከፈለው የህይወትና ሌሎች ፈርጀ ብዙ መስዋእትነትና አሁንም በትግሉ እየከፈለው ላለው መስዋእትነት በእጅጉ እናመሰግናለን። በ አማራነታችን ይበልጥ እንድንኮራ አድርጎናል። አማራነት ማለት ይህ ነው። ለሞቱት ውድ ወገኖቻችን መንግስተ ሰማያትን እንመኛለን፤ ለህዝባችንም መፅናናትን እንመኛለን። ለተጎዱትም ፈጣን ድህነትን እንመኛለን። አማራ በድል የማይጨርሰው ትግል የለም፤ ታሪካችንም የሚመሰክረው ይሄንን ነው።

በዚህ አጋጣሚ <u>በኦሮሞ ወገኖቻችን</u> ላይ የደረሰውን የሞት እልቂት ልባዊ ሃዘናችንን እንገልፃለን ፤ለሞቱት ውድ ወገኖቻችን መንግስተ ሰማያትን እንመኛለን፤ ለህዝባችንም መፅናናትን እንመኛለን!! እየደረሰ ያለውን አጠቃላይ ልዩ ልዩ ግፍ በፍፁም እናወግዛለን!!! በእንግልታችን ግዜ በጫንጩ ከተማ ላደረጋችሁልን ኢትዮጵያዊ ትብብራችሁንም በመላው የአማራ ህዝብ ስም ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

1ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ እንደሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ በጣም ሃይማኖተኛ የሚባል ህዝብ ነው፤ ቢሆንም ግን ከልቡ ያለውን እምነት መፋቅ ባይችሉም እንኳ ወያኔ ልዩ ልዩ ዘግናኝ ስራዎች በመተግበር እምነቱ እንዲጠፋ ሐይማኖታዊ እሴቱና ቅርሱ እንዲጠፋ ተደርጓል!! ታዋቂ ታሪክ አዋቂ ሙስሊም አባቶች ታስረዋል ንብረታቸው ተዘርፏል። ክርስቲያኖች ሙሉ ለሙሉ ማለት በሚቻልበት ሁኔታ የቤተ ክርስቲያኖቹ ቅርሶች እጅግ በጣም በተቀነባበረ ሁኔታ በወያኔ ካድሬዎች ተዘርፎ ለውጭ አገሮች ተሸጧል፤ ተበርብሯል እንዲሁም ታዋቂ ታሪክ አዋቂ ቀሳውስቶች ተገድለዋል። የዋልድባ ገዳምም ሳይቀር ተደፍሯል፤ ተበርብሯል። አባቶች በድብደባና በጥይት ተገድለዋል፤ የተለያየ የአካል መጉደል ደርሶባቸዋል፤ ታስረዋል እንዲሁም ተሰደዋል።

ለልማት እየተባለ ህዝቡ የእርሻ መሬቱ ከነፍሬው፣ ከብቶቹ የሚያሰማራበት ቦታውንና ቤቱን ሳይቀር ያለካሳ ተነጥቆ ምንም የጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅት በሌለበት በሃይል በወታደር እየተጠበቀ እንዲሰፍር ተደርጎ በወባና በካላዛር በሚያሳዝን ሁኔታ እንዲያልቅ ተደርጓል።

2ኛ. በወልቃይት ጠገዴ ሶስት አይነት የትግራይ ሰፋሪዎች አሉ። የወልቃይት ጠገዴ ህዝብን ሳያማክር መሬቱን እየነጠቀ በጠቅላላ ወደ 800,000 የሚሆኑ የትግራይ ሰፋሪዎች ነው በህዝቡ ላይ አምጥቶ ያፈሰሳቸው። አንደኞቹ በ1983 አ/ም የሰፈሩ የወያኔ የቀድሞ ወታደሮቹ ሲሆኑ ወደ 30,000 የሚጠጉ በዳንሻ አካባቢ እንደገና እስካፍንጫቸው አስታጥቆ ያሰፈራቸው ናቸው። እነዚህ ባሁኑ ስ አት ወልደው ከብደው ሃብት አፍርተው በህዝባችን ላይ የተለያየ አይነት ግፍ ሲፈፅሙ የኖሩ ታማኝ የወያኔ ሎሌዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በወልቃይት ጥገዴ ብቻ ሳይሆን ትግሬ ባልሆነ በማንኛውም አይነት ኢትዮጵያዊ ደስተኛ ያልሆኑ እጅግ በጣም ፅንፈኛ ተስፋፊዎች ናቸው። ባጭር አገላለፅ አማራ መጥፋት አለበት ብለው የሚያምኑ አረመኔዎች ናቸው!!! ሌሎቹ ደግሞ በ1985 አ/ም እና 1989አ/ም አካባቢ ከሱዳን የተመለሱ "ላጅን" የሚባሉ ሲሆኑ በሁመራ፣ ዳንሻ፣ ባዕከር፣ በረከት፣ ራዉያን፣ አዲጎሹ፣መተማ፣ሸኸዲ፣ አብደራፊ፣ ሽንፋ፣ ቋራና ሌሎች ሰፊ የጎንደር አከባቢዎች ያሰፈራቸው ወደ 70, 000 የሚጠጉቱ ናቸው። ሶስቶኞቹ

ደግሞ አዲሶቹ ሰፋሪዎች ሲሆኑ ከ1996 አ/ም ጀምሮ ከደጋው የትግራይ አካባቢ በዋነኝነት ከማእከላዊው የትግራይ ዞን የመጡ በብዛት <u>የታጠቁ ሰፋሪዎች</u> ናቸው። እነዚህ ሰፍሪዎች ሰርተው የሚበሉ ከሆነ ለምንድን ነው ሴቱም ወንዱም ያስታጠቃቸው? አዲሶቹ ሰፋሪዎች ከ630,000 በላይ ቁጥር ያላቸው ናቸው።በነገራችን ላይ ህዝባችን አማራ ሞተ ሲሉ በተለይ ደግሞ አማራ የተቀበረው በወልቃይት ነው ከሩብ ምእተ አመት ብኋላ ጀግናው ህዝባችን እኔ አማራ ነኝ ብሎ ሲነሳ ወገባቸው ለሁለት ነው የተከፈለው። አቶ ኢሳያስ ታደሰ የተባለው በወልቃይት ውስጥ በሁመራ የዞን አስተዳዳሪ ሆኖ የተሾመው የህወሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባል እንደተናገረው ቀበርነው ያለነው አማራ እንዴት ገዳይ ሆኖ ተነሳ ነበር ያለው። ለእኛ ይህ ትልቅ ታሪካዊ ንግግር ነው። አዎ አንተ እንዳለከው "የሞተው አማራ ገዳይ ሆኖ ነው የሚነሳው!!!"። <u>"የወልቃይት ጠገዴ አማራ ማንነት ጥያቄ የተነሳው ሰፈራው በቆላ አካባቢ ብቻ የተከናወነ ስለነበር የባህል ትስስር ባለመፈጠሩ ምክንያት የመጣ ነው"</u> ብለው በማሰብ ግልፅ የሆነውን የማንነት ጥያቄያችን የመልካም አስተዳደር ችግር ነው ብለው ጥያቄያችንን ሲያዳፍኑት ሞከሩ፤ ከዛም ደግሞ ወደ ደጋው የወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ተጨማሪ ሌላ 70 ሺ ትግሬ ለማስፈር እቅዱን አቅደው ለተግባርዊነቱ መዘጋጀታቸው በስብሰባቸው ውሳኔ አሳለፉ። ነገር ይህን ደካማ አስተሳሰብ ያሰቡት እንደተናገሩት የሞተ አማራ እንዴት አፈሩን አራግፎ ሊነሳ ቻለ የሚለውን ጥያቄ ስላስደነበራቸው ነበር። ስለዚህ እውነቱን መቀበል ስላልፈለጉ የሚያስቡት መፍትሔም መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ለማንኛውም ችግር የለም ይምጡ ፤አዎ ለመተራረድ ይምጡ!!! ከእንግዲህ ብኋላ የኛን መልካም ነገር ላያዩ ይምጡ። ገዳዮቻችን የምናስተናግድበት ምንም አይነት ግዴታ እንደሌለብን በዚህ አጋጣሚ በልበ ሙሉነት ልንገልፅላቸው እንወዳለን!!!

እዚህ ላይ ለወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በጣም አስደንጋጭ የሆነው ነገር <u>የሶስትዮሽ ጎን የአሰላለፍ ዘመቻ (Triangular Campaign)</u> የሚባል ሚስጥራዊ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ የማጥፋትና የታላቂቷ ትግራይ የተስፋፊነት ህልም እውን የሚያድርግ እቅድ ይዘው ነው የተነሱት። አሰላለፉ እንዴት ነው ቢሉ አንደኛው መስመር ትግራይን ተሻግረው ከተከዜ እስከ ሁመራ በ15 የሰፈራ ማእከሎች የሰፈሩ ሲሆኑ ከጥርጊያ በታች

የወልቃይት ሰው እንዳይወድ በማድረግ ወደ ደጋው እየገፉ የሚወጡ ተስፋፊ ነጻ አውጭ ቡድን ናቸው። ሁለተኛው መስመር ደግሞ በሁመራ አከባቢ ያሉ አዳዲስ ከተማዎች ማቋቋምን ጨምሮ ከሁመራ ዳንሻና ሹመሪን ጨምሮ እስከ የጎንደር ድንበር ሶሮቃ ድረስ ጥርጊያውን ተከትለውና ከጥርጊያው በታች በሙሉ የሰፈሩ ሲሆኑ እነዚህም ከድሮ ሰፋሪዎች ጋር አንድላይ በመሆን የእርሻና ከብት ማርቢያው ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር ወደ የወላቃይት ጠገዴ ደግማው አከባቢ በሂደት እየገፉ የሚዘልቁ አደገኛ ቡድኖች ናቸው። አሁን በዚህ አንድ አመት ያቀዱት ደግሞ ከሰሮቃ በሳንጃ በኩል እስከ ትክል ዲንጋይ ድረስ በተለያየ መንግድ በህቡእ ለማስፈር አስበዋል። ይሄን እውን ለማድረግ ካሰቡበት መንገድ አንዱ *ባለሃብት ትግሬዎች በልዩ ልዩ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም <u>የኮንዶሚኒየም ግንባታ፣ ሆቴል፣ ቡቲክና የመሳሰሉ "ልማታዊ " እንቅስቃሴዎች</u> በሰፊው እንዲሳተፉ በማድረግ አካባቢውን በከፍተኛ ሁኔታ በመቆጣጠር* ትግሬያዊ ለማድረግ ያለመ ነው። ይህ አካሄድ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡብ ት ሲሆን ከወልዲያ እስከ ሸዋና ባህርዳር ድረስ የሚደርስ ነው። ሶስተኛው መስመር ደግሞ በአጭር ግዜ ውስጥ ወልቃይት ጠገዴን ህዝቡን አጥፍቶ ለመቆጣጠር "<u>የመጨረሻው የድል መስመር</u>" ብለው የሚጠሩት ከሽሬ ጀምሮ ወልቃይት ጠገዴን ለሁለት ከፍሎ ሱዳን ድረስ የሚወስደው በፍጥነት ያለቀው እጅግ በጣም ዘመናዊው የአስፋልት መስመር ተከትለው ማንም ሳያውቅ የሰፈሩ በጣም ጥጋበኛና ግፍ ፈጻሚ ተስፋፊዎች የሰፈሩበት ነው። ይህኛው መስመር አንድም ወልቃይት ጠገዴን ለሁለት ከፍሎ እንዳይገናኙ ለማድረግ ይልቁኑ በአዳዲስ የሰፈራ ከተሞች ምክንያት በማድረግ ወደ ወልቃይትና ጠገዴ ከላይኛው የደጋ በኩል ወደ ቆላዎቹ ቦታዎች በመግፋት በቆላዎቹ ከሚመጡ ተስፋፊ ቡድኖች ጋር በቀላሉ ለመገናኘት የታሰበ እጅግ በጣም ቀጥተኛውና አደገኛው የሞት መስመር ነው። ይህን የጥርጊያ መስመር እንዲሰራ አንፈልግም ያሉ ከ129 በላይ የወልቃይት ጠገዴ ሰዎች ታፍነው ከተወሰዱ ብኋላ እስካሁን ድረስ የት እንዳሉ አይታወቅም። ይህ መስመር እጅግ በጣም አዉዳሚ መስመር ነው። ከዚህ በተረፈ ወልቃይት በሚገኘው የስኳር ፋብሪክ ፕሮጀክት አማካይነት የሰፈሩ ከ30,000 በላይ አተራማሽ ተስፋፊ ቡድኖችም በህዝቡ ህልውናና ንብረት እንዲሁም ተፈጥሯዊ ሃብት ያደረሱትና እያደረሱት ያሉት ጭካኔና ግፍ ለመናገር ሌላ ጽሑፍ የሚጠይቅ

ነው። እንግዲህ በዚህ መልኩ ነው ወያኔዎች የወልቃይት ጠገዴ ህዝብን እየገደሉ፣ እያሰሩ፣ እያሰደዱ፣ እያፈናቀሉ፣ ንብረቱን እየዘረፉና ተፈጥሯዊ ሃብቱን እየጨፈጨፉ ለመስፋፋት እየሞከሩ ያሉት!!! ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሆይ ስቃያችንን ተመልከቱ፤ ይህ የአስተዳደር ችግር አይደለም የማንነትና የህልውና ጉዳይ ነው እንጂ። አማራነታችን እንዲከበርና ለዘር የሚተርፍ ትውልድ እንዲኖረን እርዱን ድረሱልን!!!

ኢትዮጵያዉያን ወገኖቼ ሆይ ስለዚህ ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳት በቅርቡ "የህወሓት ሴራ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ" የሚል ከእጃቸው በአገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን የተጋለጠው ሴራዊ ዶክመንት እንድታነቡ በትህትና እጋብዛለሁ። ይህ ጽሑፍ በድረ-ገጽ ታገኙታላችሁ።

ከአብዛኞቹ የሱዳን ተመላሾች በቀር ሰፋሪዎቹ ብዙ ግዜ ነገር ነገር የሚሸታቸውና ታጥቀው የሚጓዙ ናቸው። ከህዝቡ ጋር ይጣላሉ፣ አንዳንዴም ሴቶችን ይደፍራሉ፣ የህዝቡን ከብትና በግ ዘርፈው ወደ ሱዳን ይሸጣሉ። ለህዝቡ ፍጹም በጥላቻ መነጽር ብቻና ብቻ የሚያዩ ናቸው። ምን አይነት የጥላቻ የፖለቲካ ትምህርት ለስንት ግዜ በምን አይነት ሁኔታ እንደተሰጣቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው። ከጥርግያ በታች ወይንም ቆላው አካባቢ የነበሩ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ንብረቱ የሚያቆይባቸው ቦታዎች ሁሉ ለእነዚህ ሰፋሪዎች ስለተሰጠ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ንብረቱንም ስለሚዘረፍበት ህዝቡ ያለው አማራጭ ንብረቱን በዋነኝነት ከብቶቹ፣ በጎቹና ፍየሎቹ መሸጥ ስለሆነ ንብረቱን ሸጦ ከተማ ገብቶ አንዳንድ የኑሮ እንቅስቃሴ ሲጀምርና የተካነበት የእርሻ ሙያውን ባለችው መሬት ማረሱን ሲቀጥል በተለያይዩ ምክን ያቶች ተስፋ እንዲቆርጥ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው ሁሉ ያለምንም ተቀናቃኝ በቆዩና በአዲስ ሰፈሪዎቹ እንዲሁም በአዲስ ከትግራይ በሚመጡ ሰፋሪ ያልሆኑ የትግራይ ልጆችና የባለስልጣን ዘመዳሞች ቁጥጥር ስር ወድቋል። የወልቃይት ጠገዴ ህዝብም ይህ ወልቃይት ጠገዴ እኮ እኛም ተወልደንበታል ኢትዮጵያውያን ነን ሲል "እንኳን ቆላው ደጋውና ሴቶቻችሁ ገና እንረካበአችኋለን" በማለት ህዝቡን እንደ ቁሳር መንግስት ያስጨንቃሉ። በዚህ መልኩ ህዝቡ

ነፍጥኝነት ሲያነሳ ቤተሰቦቹን የነፍጠኛ ዘር እያሉ ሲጨርሱት ስለቆዩ በራስ ላይ ሞት ከማምጣትና ቤተሰብ ከማስጨረስ በቀር ምንም ለውጥ እንደማያመጣ ከባለፉት ግዝያቶች በህይወቱ ስለተማረ ምንም እንኳን ውስጡ ባይሸነፍም የበይ ተመልካች ሆኖ እየኖረ ይገኛል።

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ የሚሰራው ግፍ በዞህ ብቻ የሚያበቃ እንዳይመስላችሁ ከታች ለመጠቃቀስ እንደሞከርኩት እንዲህ እየባሰ ክፋቱና መልኩ እየቀያየረ እየቀጠለ ነው እንጂ።

3ኛ. ሴት ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸው፣ በወታደሮቻቸው፣ በግብርናና በህክምና ባለሙያ ነን ባዮችና ጓደኞቻቸው ገና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ ይደፈራሉ፣ ያረግዛሉ፣ ትምህርት ያቋርጣሉ፣ ይኮበለላሉ። አሳዛኙ ነገር ይሔን የሚያደርጉት የትግራይ ሰዎቻ አብዛኞቹ በትግራይ ባለትዳርና ባለልጅ መሆናቸው ነው። እንዲህ አይነት አጸያፊ ስራ በህዝባችን እንደነውር ስለሚቆጠር የተደፈሩ ህጻናት ልጆች ለቤተሰቦቻቸው ያጋጠማቸው የልብ ስብራት አይናገሩም አንድም ቢናገሩ በደፋሪዎቹ ቤተሰቦቻቸው አንድ ነገር ቢያደርጉ ቤተሰቡ እንደሚፈርስ በማሰብም ዝም የሚሉ አሉ፣ አንዳንዶቹ ራሳቸውን ያጠፋሉ ሌሎቹ ደግሞ ካራገዙ ብኋላ እውነቱን ይናገራሉ።

አብዛኞቹ ይህን መከራ የደረሰባቸው ለጋ ህጻናት ከወላጆቻቸው ጋር ተጣልተው ትምህርታቸውን አቋርጠው አባት የሌለውን ልጅ ታዳጊዎቹ አሳዳጊ ይሆናሉ። ምንም እንኳን በመጨረሻው ቤተሰቦቻቸው አዝነው በዝሙት ተዳድረው ከሚኖሩ ብለው ቢቀበሉዋቸውም በቤተሰብ ውስጥ ግን ሰላም የለም። ወንድ ተማሪዎችም የተለያዩ ምክንያት በመፍጠር መምህራኖቻቸው ትምህርት እንዲያቋርጡ ያደርጋሉ።

ይህን ሁሉ ግፍ ለሚያደርጉ በህግ ተጠያቂ እንደማድረግ የሚበቃውን ወንጀል የፈጸመን አካል ቦታ በመቀየር “አበጀህ” በሚል ስውር የሞራል አሰጣጥ የተሻለ ስልጣንና ደሞዝ ተደርጎላቸው በትግራይ የአስተዳደር ስራ ውስጥ ይቀመጣሉ አንዳንዴም በአከባቢው ይሾማሉ።

ለምሳሌ ይሆነን ዘንድ የዚህ ችግር ቀማሽ የሆነችው አታላ የተባለች የ13 አመት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ከዳንሻ ከተማ መጥቀስ ይቻላል። አስተማሪዋ ከደፈራት ብኋላ ደብድቦ የስነልቦና ጫና በማሳደር ፍርሃት እንዲሰማት ካደረገ ብኋላ ህጂና ከቤተሰብ ብር ሰርቀሽ ነይ ይላታል። ልጅቷም ሃብታም ቤተሰብ ስለ ነበሯት ሳጽን ሰብራ 60,000 ብር ወስዳ ከሰጠችው ብኋላ አፍኖ ወደ ትግራይ ወስዶ የሚፈልገውን ሁሉ ከፈጸመ ብኋላ ሆቴል ውስጥ ያስቀጥራታል። ለምን ስትለው ባለትዳር እንደሆነ ነግሮ ወደ አግርሽ ጥፌ ብሏታል። በቤተሰቡ ሊደርስ የሚችለው የልብ ስብራትና የሰላም መጥፋት ምን ሊሆን እንደሚችል ለእናንተ እተወዋለሁ። ህጻኗ እንዴት ወደ አገሯ መመለስ እንዳለባት እንኳን አታውቅም ነበር! የጭካኔው ብዛት ምክን ያቱ ምን እንደሆነ ባናውቅም ካስረከበችው 60 ሺ ብር እናኳን ለመሳፈሪያ የሚሆን ሰጥቶ ቢልካት ምን ነበረበት? ተመሳሳይ ችግር የደረሰባቸው ልጆች እግዚአብሔር ይቁጠራቸው። ታዳጊዎቹ አቻዥ የሌላቸውን ዲቃላ ህጻናትን እያስረከቡ ማህበረሰቡ ላይ ነገ "አባቴ" የሚል ሰው መሳይ መርዝ ችግኝ እየተከሉ ይሔዳሉ፤ በጣም ያማል ወገኖቼ!!! የወልቃይት ጠገዴ ህዝባዊ ስብጥሩ በግድ ለመቀየር (Genocidal Demographic and Social Engineering) የሚያደርጉት ታሪክ ይቅር የማይለው ሰይጣናዊ ድርጊታቸው ነው። ለዛውም የህዝቡን ህልውና የካዱ የሰይጣን መንፈስ የሞላባቸው ከንቱና እርጉማን ሰዎች!!! በዚህ ጉዳይ በቅርቡ ዘግቤ አጋልጨ አስነብባችኋለሁ፤ ግፍን ማጋለጤን እቀጥልበታለሁ፤ ከዛ ብኋላም ብሞትም እንኳን ደስ ብሎኝ ነው እምሞተው። ህዝቤንና አገሬን የሚታደግ ስራ ሰርቼ ስሞት ለእኔ የክብርም የደስታም ሞት ነውና። ድሮስ ሰው የተሰራው ፈራሽና በስባሽ መሆኑ መች አጣሁትና!!! ለመወሰን አንቸኩልም እንጂ ቆርጠን ከተነሳን ደግሞ ማን እንደሆንና ወደኋላ እንደማንል በደምብ ያውቁናል፤ ፈጣሪም ከእኛ ከጭቁኖቹ ጋር እንዳለ በፍጹም መተማመን ሆነን በሙሉ ልብ እንናገራለን። እኛ ግን ከህሊናችን ጋር ስላለን የማንነት ጥያቄው ይመልሳሉ ብለን አሁንም ቢሆን በትዕግስት እየጠበቅናቸው ነው፤ ካልሆነ ግን በአማራ ማንነት መጠየቅ ምክንያት በግፍ የታሰሩት ሁሉም የወልቃይት ጠገዴ ወገኖች፣ በሰሜናን ደቡብ ጎንደር፣ በባህርዳር፣ በደብረማርቆስ፣ በሰሜናን ደቡብ ወሎ፣ በሸዋ እና መላ አማራ ያሉ አማሮች ባስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ካልተፈቱ፣ የሞቱት ሰዎች ካሳ

ካልተከፈሉ፣የተጎዱ ሁሉም ካልተካሱና  የአጋዚ ጦር ባስቸኳይ ከክልላችን ካልወጣ ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንደምናመራ የተረጋገጠ እውነት ነው!!! መስሏችሁ ነው እንጂ ህዝባችንን ወደባሰ እልህና ቁጭት እየመራችሁት ነው ያላችሁት ደግሞም በሃይል በአፈና አሁን ባለው መልኩ እኛን ማንበርከክ አትችሉም፤ እንደማትችሉም ታውቁታላችሁ። በአለም ዙርያ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሆይ የማንነት ጥያቄያችንን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲመልሱልን እርዳታችሁ አይለየን።

4ኛ. ይሔን ሁሉ ፈተና አልፈው ዩኒቨርስቲ ወይንም ኮሌጅ ገብተው የተመረቁ አንዳንድ የወልቃይት ጠገዴ ልጆች በመንግስት ስራ አይመደቡም ቀደም ብለው የተመደቡትም ሙቶ በሙቶ ማለት ይቻላል ከተመደቡበት ስራቸው ተባረዋል። የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሁሉ በአድዋ ልጆች አለፍ ካለም በአክሱም ልጆች ተተክተዋል። አንዳንድ በስራ የሚገኙ በዲፕሎማ ሙያ በአስተማሪነት ቢመደቡም እነዚህም ባሎቻቸው ፖሊስ ወይንም ስልጣን ያላቸው የትግራይ ተወላጆች ከሆኑ ብቻ ነው።

አንዳንድ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ፖለቲካዊ ማግለሉና አስተዳደራዊ ጫናው ተቃቁመው ለመስራት ቢወስኑም ጫናውና ማስጠንቀቂያው ከባድ በመሆኑ ወይንም በራሳቸው ስራቸው ለቀው ያለስራ ይቀመጣሉ ወንም ደግሞ በአድዋና አክሱም አለቆቻቸው ይግባኝ በሌለው የስንብት ደብዳቤ ይሸኛሉ። አይ የመጣ ይምጣ ብለው ለማስራት ወስነው የነበሩ ጥቂት የመንግስት ሰራተኞችም ወንጀል ሰርተዋል ተብለው ማረሚያ ቤት የገቡም ነበሩ፤ አሁንም ያሉ አሉ።

5ኛ. ከላይ በ ተራ ቁጥር 4 እንደነገርኳችሁ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሙቶ በሙቶ በአድዋና በአክሱም ተወላጆች የተያዙ ናቸው። እናም የተለያዩ አስተዳደራዊም ሆነ ግላዊ ችግር የደረሰባቸው የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች “የመንግስት ያለህ” ብለው ብሶታቸውን ለማሰማትና ፍትህ ለማግኘት ሲሔዱ ገና በንግ ግራቸውና በቋንቋቸው ለዛ ስለሚያውቋቸው እንኳን ብሶታቸው ሊሰሙላቸው ሌላ ችግርና ብስጬት መርቀው ይመልሷቸዋል። በጣም ተናዶ ለሄደ ወጣት ወይ ጎልማሳ ሰው በተካኑበትና ሴራ በተሞላበት መፍትሔ በሌለው “ችግሩን እናየዋለን” ወይንም የኔ ቢጤ አቅም የሌለው ሰው ከሆነ

ደግሞ በማሬዝ ፍትህ አጓድለው ህዝቡን እግዚአብሔር የሰጠውን ነጻነቱን ነፍገው በሓዘንና በቁጭት እንዲኖር አድርገዋል። የ80ና የ90 አመት አዛውንት በደረሰባቸው ችግር እንኳን ልጆቻቸውን ወክለው መከሰስና መሟገት አይችሉም፤ ነገሩ ከምነግራችሁ በላይ እጅግ በጣም አሳዛኝ ነው።

ብዙ ግዜ <u>“ለምን እንዲህ ይሆናል፤ ለምን እውነትን ትግደሏታላችሁ ተው ኧረ ተው ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ይሔ ነገር አይጠቅማችሁም ለእኛም አይበጅ!!!”</u> ብለው የተናገሩ አባቶችና እናቶች ከዚህ መጡ በማይባሉ ፖሊሶች ታፍነው ይጠፋሉ። ኧረ “እንትና የት ገባ?” ሲባል ከተወሰኑ ሳምንታት፣ ወራት ወይንም አመታት ብኋላ ኧረ “እሱማ/እሷማ መቀሌ ማረሚያ ቤት እኮ ነው ያለው” ይባላል። ማን ከሶት ታሰረ? ለስንት ግዜ ነው የተፈረደበት? መልስ የለም። ኧረ ለመሆኑ ለምንስ እዚህ ቤተሰቦቹ ባሉበት አላሰሩትም? ኧረ እንዲያው ምንስ ብለው ነው ያሰሩት? አሁንም መልስ የለም። በነገራችን ላይ ቤተሰቦቻቸው እንዲጠይቋቸው የሚፈቀድላቸው አይሆንም።

6ኛ. አንዳንድ ባለቻቸው ንብረት በግላቸው በንግድ ስራ የሚንቀሳቀሱት የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ገቢን መሰረት ያላደረገና በጣም ከፍተኛ የግብር ክፍያ አንዳንዴም ከጠቅላላ ካፒታላቸው በላይ የሆነ ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ከገብያ ውጭ ሆነው በብስጭት እንዲታመሙና ራሳቸውን እንዲያጠፉ ይደረጋሉ። ለገሚሶቹ ደግሞ መሰረትነት በሌለው የውንጀላ ስራዎችና ማስፈራሪያዎች ተደርጎባቸው የንግድ ስራቸው እንዲዘጉ ይደረጋሉ ይታሰራሉም። በዚህ መልኩ ከጨዋታ ውጭ ይደረጋሉ!! ከዛም ቤተሰቦቻቸው በሓዘንና በብስጭት እንዲሁም በእጦት ምክን ያት በአይነቱ ልዩ ልዩ ወደ ሆነ ስቃይ ገብተው እንዲኖሩ ይደረጋሉ።

እዚህ ላይ በወልቃይት ጠገዴ የሚሰሩት ከዚህ ጋር የተያያዘ ግፍ በጥቂቱም ቢሆን መንገር የግድ ይለኛል። በንግድ ሙያ የገቡ እነዚህ ሰፋሪ ትግሬዎቹ በጣም ሃብታም ናቸው። ሃብታም የሚሆኑት ታድያ በወራት ውስጥ ነው፤ ግብር አይከፍሉም ልዩ ብድር ይመቻችላቸዋል። በአመት ውስጥ ከተማ ውስጥ ሶስት አራት ቦታ ላይ ቤት የሚሰሩና ባለመኪና ናቸው እነዚህ ሰፋሪዎች ናቸው። ወደ ጉዳይ እንመለስና እኒህ ሰፋሪ

ነጋዴዎች ምን ያደርጋሉ ብትሉኝ ከላይ በጠቀስኩት አይነት ከፍተኛ የግብር ክፍያ የሚሰቃዩትን የወልቃይት ጠገዴ ነጋዴዎችን ጭንቀታቸውን ያዩና ቀረብ ብለው "አንተ ሞኝ ነህ እንዴ፤ለእኔ እኮ እንዳንተ ከፍተኛ ግብር ከፈል ብለውኝ ይሄን ያህል ለሻይ ይሁንህ ብየ ስሰጣቸው አንድ ሶስተኛውን ብቻ ነው ያስከፈሉኝ" በማለት ሹክ ብሎ ተወላጆቹ ሙስና እንዲከፍሉ ያበረታታቸዋል። ሌላ መንገድ እንደሌለ እቅጩን በዚህ መልኩ ይነገራሉ ፤ በህግ እሔዳለሁ የሚል ተወላጅ ካለ በተራ ቁጥር 5 የገልጽኩት ሂደት እንዳለ ስለሚያውቁ ለተደገሰላቸው የሙስና ጥያቄ ለዛውም ተሸማቀው እንዳይያዙ በመፍራት በጭንቅ ደጅ ጠንተው ህሊናቸው ሳያምነበት ከራሳቸው ጋር እየተጣሉ ይከፍላሉ። አብልግ ወይ በሰርግ የተዛመዳቸው ካለ ከእንደዚህ አይነት ስቃይ ነጻ ነው ግን እንዲህ ያደረጉ ትንሽ ተወላጆች ናቸው። ይህ ለምን ይደረጋል ብትሉ  ፈቅዶ ስለማይዛመዳቸው በግድ እንዲዛመዱት ለማድረግም ጭምር ነው። ዋናው አላማ ይህ ቢሆንም ከርሳቸውም ለመሙላትም ጭምር ነው እንጂ።

እንዲህ ከሚሉት የተወሰኑቱ  የሙስና በይዎቹ ቀንዳኛ ወዳጆች፣ ደላሎችና ተጠቃሚም ናቸው። ሌላው ከግብር ጋር በተያያዘ የሚሰሩት ድራማ ደግሞ ለሰፋሪዎቹ የትግራይ ተወላጆች "ይህን ያህል ብር በዚህ ግዜ ወደ ቢሮ ገቢ ካላደረክ ከዛሬ ጀምሮ የንግድ ስራህ ታሽጓል" ብለው ይዘጉቧቸዋል፤ ተመሳሳይ የንግድ ዘርፍና ካፒታል መጠን ያላቸው የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆቹንም እንዲሁ ካደረጉ ብኋላ የትግራይ ሰፋሪ ተወላጆቹን የግብር መጠን ግን ከፍ ያደርጉባቸዋል። እንዲህ የሚያደርጉት የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ነጋዴዎች ግብር የመከፈል ችግር ኖሮባቸው ሳይሆን ያለምንም ድርድር ከፍተኛው የግብር ተመኑ እንዲከፈሉ ለማድረግ ነው፤ ከዛ የትግራይ ተወላጆች እየተጣሉ እየተጨቃጨቁ ከተወላጁ በላይ እንዲከፍሉ ካደረጓቸው ብኋላ ለትግራይ ተወላጆች ብሩ ይመለስላቸዋል።

እንዴ በጣም የሚያስደንቅ እኮ መአት ነው የተጣለብን፤ በሁለትና ሶስት ትራክተር ሲያርሱ የነበሩ ኢንቨስተር ተወላጆች በዚህ መልኩ ደህይተው የተተመነላቸው ከፍተኛ ህገወጥ ግብር መክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት ወደ ሱዳን ሲሰደዱ በየወሩ በየቤቱ እየዞሩ የዉሃ ሒሳብ የሚያስከፍሉ የትግራይ

ተወላጆች ደግሞ በአንጻሩ ባለ ሁለት ፎቅ ቤት አሰርተው አከራይተው ሲኖሩ ታያላችሁ በጣም አይን ያወጣ ኢኮኖሚያዊ ዘመቻ (economic ‘genocide’) እኮ ነው።

እግዚአብሔር ያሳያችሁ ወገኖቼ ከሞት ከእስራት የተረፉት የወልቃይት ጠገዴ አማራ ህዝብ በምን አይነት ስቃይ ህይወታቸው እየመሩ እንዳለ!! ከእነዚህ ሰዎች ጋር ነው 25 አመታቶችን ሙሉ የኖርነው፤ እነዚህ ሰዎች እኛን ትግሬ ናቹህ የሚሉን ማርና ወተት የምናፈልቅላቸው የሰውም የምድርም ከንዓን ስለሆንላቸው ነው እንጂ አማራነታችን እኮ ከኛ በላይ ሲመሰክሩልን ነው የኖረነው። ይሄ ሁሉ አልፎ ትውልዳቸው መቀጠሉ እንደማይቀር በማሰብ እንኳ ለትውልዳቸው ጥንቃቄን የማያደርጉ ልክፍታም ገንዘብ አምላካቸው የሆነባቸው የዘመናችን ቀዳሚ እርኩሳን የሴጣን መንፈስ የሞላባቸው እርጉማን ሆነዋል፤ ያሳዝናል በውነት። ታድያ እኛ ከእነርሱ ጋር ስንኖር ከሞቱት በላይ በዚች አለም ካሉት ሰዎች ሁሉ በታች ሆነን ነው። የግፋቸው ግፍ በተወልደንበት ምድር በሰፈራ መጥተው አገራችንን ውጡልን አሉ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ግን ይህ ግፍ ላይቀጥል ባንድ ልብ ተነስተናል!!!

7ኛ. የትኛውም አይነት ክፍት ስራ በመንግስት መስሪያ ቤት ካለ ብዙ ግዜ የስራ ማስታወቂያ ሳይለጠፍ ወገናቸውን ያስገቡበታል። የስራ ማስታወቂያ የሚለጠፍ ከሆነ ደግሞ ስራው ካለበት ከወልቃይት ጠገዴ ውጭ በትግራይ ከተሞች ነው የሚለጠፈው። አንዳንዴ ቀለል ላሉ ግዜያዊ ስራዎች ለምሳሌ ለጉልበት ስራ ኩንትራት እዛው አካባቢው ላይ ቢለጥፉም የሚላስ የሚቀመስ የሌለው በጣም ድሃ የተባለ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ሄዶ እንኳን አያመለክትም። የሆነ ግዜ ላይ ለእንደዚህ አይነት ስራ ሊያመለክት የሔደን የአካባቢው ተወላጅ ምን ልታደርግ ነው የመጣኸው ተብሎ በመዝጋቢዋ ተሹፎበታል። የቅጥር ዉሳኔው ከውድ ድሩ በፊት ማለትም ከምዝገባው በፊት በድፍረት እንዲህ ይናገራሉ!!! የትግሬዎቹ ጥጋብ እጅግ በጣም ልኩ ያለፈ ነው። ይህን የሚያደርጉት እኛ ተማረን አገራችን ጥለንላቸው እንድንሔድ ነው። በነገራችን ቅንጣት ሰብአዊነት የሌለባቸው እጅግ በጣም አሳዛኝ ስግብግብ የተራቡ አንበጣዎች ናቸው፤ አዎ አስገራሚ “የሰው አንበጣዎች”።

8ኛ. በወልቃይት ጠገዴ ተወላጅና ነገር ነገር በሚሸታቸው እንዳበደ ውሻ በሚክነፈነፉት የትግራይ ተወላጅ ወያኔዎች መካከል ተወላጁ ትዕግስቱ ተሟጦበት ችግር ከተፈጠረ ያለምንም ማጣራትና ያለምንም ምንም ጥርጥር ለትግራይ ተወላጁ ስለሚፈረድለት ብዙ ግዜ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ከእነርሱ ጋር በሰቀቀን ነው የሚኖረው፤ አመላቸው ራሱ የምትይዘው የምትጨብጠው አይነት ስላልሆነ ተወላጁ የቤተሰቦቹን ሰላም ለመጠበቅ ሲል ትንኮሳቸውን በመፍራት በጣም ርቋቸው ነው የሚኖረው። ለንግድና ለኑሮ የመጡ ትግሬዎች እንኳን ሲቪል ቢምስሉም አላማቸው ግልጽ ያልሆነ የፈርዖን አብጋዞች ናቸው። የሚደንቀኝ እርስ በርሳቸውም እንዲሁ ነው የሚበላሉት! አዎ ፍቅር የሚባል ነገር በመሃላቸው የለም፤ አንድ የሚሆኑት በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ብቻና ብቻ ናቸው። እናም የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በሃገሩ ወንጀል እንደሰራ አይነት ህዝብ ሆኖ እንደሁለተኛ ዜጋ በቁም እስር ነው የሚኖረው። ይህ በራሱ የሚያሳየው እነርሱ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ እንደጠላታቸው ማሰባቸው ለወረራ መምጣታቸውና በግድ እኛን ትግሬ ለማድረግ ስላልቻሉ አላማቸው ባለመሳካቱ ምክን ያት የመጣ ንዴታቸው ነው፤ አማራነታችን ብንፈተንበታም ገና አንገታችን ቀና ብሎ ኮርተንበት በደስታ እኖራለን። አዎ አማራነት ወንጀል አይደለም አማራነታችን ይከበረልን!!!

9ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በአያቶቹና ቅድመ አያቶቹ የመሰረቷትን የሁመራ ከተማ ውስጥ ወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ማግኘት እንደትልቅ የምስራች የተቆጠረበት የግዜ ደፊ ላይ ነው የምንገኘው፤በቃ ያለነው ጥቂት ተወላጆችን ስንገናኝ በሓዘን ድባብ ሆነን ቆይ ግን ይህ ሁሉ ህዝብ በምን መልኩ ነው የጨረሱን ተባብለን እንላቀሳለን። ከዚህም የተነሳ ሰፋሪ ትግሬዎቹ የልብ ልብ ተሰምቷቸው ሁመራ የኛ ናት በማለት የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅን ጸጉረልውጥ ይሉታል። ምናለ ሁመራን የሁላችን ነች ቢሉ እንኳ። በተለያየ ግዜ በተለያየ የኢትዮጵያ ቦታ በዋነኝነት ከአዲስ አበባና ጎንደር ቆይተው የሚመለሱ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆችን ሲያዩን "ፀጉረ-ልውጥ" አይተናል ብለው ለፖሊሶቻቸው በነፋስ ፍጥነት ሄደው ሪፖርት ያደርጋሉ። ፖሊስ ነን ባዮችም እኛን ተወላጆችን ይዘው "አንተ ማን ነህ"፤ "ከየት መጣህ"፤ "ለምን መጣህ" እያሉ ካዋከቡና የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች መሆናችንን ካረጋገጡ ብኋላ "አንተ የመስፍን ዘር" ፤ "አንተ

የነፍጠኛ ዘር" ብለው ያንገራግራሉ፣ ይሳደባሉ፣ ያስፈራራሉ፣ ይደበድባሉ እንዲሁም ያስራሉ። እንዲህ ስለሚያደርጉን ብዙ ግዜ ወደ ቤተሰቦቻቸው የማይመለሱ ብዙ ናቸው። "ምን ሆንክ? ይህ እኮ ትግራይ ነው!" ይልሃል ፖሊሱ። በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው በአገራችን መኖሪያ እንጣ። በነገራችን ላይ በዚህ መሃል ያለ ውጣ ውረድና ወከባ ተዉት። ይህ እውነታ በሁሉም የወልቃይት ጠገዴ አካባቢ የነበረና አሁን ደግሞ በባሰ ሁኔታ ያለበት ችግር ነው። እኛ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች ማንነታችን የሚያረጋግጡበት መንገድ በመታወቂያችን ሳይሆን ወላጆቻችና የሚታወቁ ቤተሰቦቻችንን ፖሊስ ጣብያ ጠርተን ካመጣን ብኋላ ነው። ይህ ጉዳይ ለእኛ ከፍተኛ የሆነ ስነልቦናዊ ስብራት ነው አብሶ ደግሞ ለወላጆቻችን!!! ይህ ችግር በቋንቋ ከምገልጸው በላይ በጣም በተቀነባበረ ሁኔታ ነው የሚፈጸመው። በልዩ ልዩ ስራና በትምህርት ምክን ያት ከአካባቢው ርቀው የቆዩ ሰዎች መታወቂያችንን ለማደስ የማንችልበት ሁኔታ ነው ያለው። ይህን የሚያደርጉት ህጋዊ ኗሪ አይደለህም ለማለትና ከአካባቢው እንድንለቅ ለማድረግ ታስቦ የሚፈጸም ዘግናኝ ድርጊት ነው።

በጣም አሳዛኙ ነገር ፖሊሶቹ በራሳቸው ለአካባቢው አዲስና በእነርሱ ቋንቋ ከዚህ በተያያዘ ታድያ በየቀኑ አዳዲስ የትግራይ ተወላጆች ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ተመልከቱ በእነርሱ የወረደ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ የዘረኝነትና ተስፋፊነት ቋንቋ እንድናገር አንዴ ፍቀዱልኝና "ፀጉረ-ልውጥ" እነርሱ ሆነው ሳለ እኛን ተወላጆቹን "ፀጉረ-ልውጥ" ብለው ያንገራግራሉ!!! የአካባቢው ተወላጆች ሌላው ቀርቶ 25 አመት ሙሉ የመኖሪያ ጎጇቸውን የሚሰሩበት ቦታ እንዲሰጣቸው እድሜ ልካቸው ጠይቀው ያልተሰጡ እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሰፋሪዎች የትግራይ ተወላጆች ግን ተወላጆቹ ገና ስማቸው እንኳን ሳያውቅ ከመኖሪያ ቤት ባለቤትነት በዘለለ በተለያዩ የልማት አደረጃጀት በሌላ አገላለጽ የፖለቲካ አደረጃጀት ተደራጅተው በወራት ውስጥ ሃብታም ሆነው የህዝቡ ፈላጭ ቆራጭ ሆነው ማየቱና ከዚህ በላይ ደግሞ የፍትህ ማጓደላቸው ስራቸው ስትታዘቡ እንዴት ያማል መሰላችሁ። በነገራችን ላይ የአካባቢው ተወላጅ የሆነ ማንም ሰው ወደ እንደዚህ አይነት አደረጃጀት እንዲገባ አይፈቀድለትም ህዝቡም ደግሞ በፍጹም መግባትም አይፈልግም። ህዝቡን ተገልብጠው "አንተ ማነህ" የሚሉት እነዚህ የቀን ሃብታሞች የሆኑ ዘራፊና ወራሪ

“ኢትዮጵያውያን” ነን የሚሉ “የትግራይ ሰዎች” ናቸው። ግዜ አንገት ደፊ ያደርጋል፤ በእርግጥ የእኛ አንገታችን ብቻ ሳይሆን ስብእናችንንም ሕይወታችንም ለማስደፋትና ለመድፋት ጥረዋልም ይጥራሉም ግን ግን ከአሁን በፊትም አልቻሉም ከአሁን ብኋላም አይችሉም እንጂ፡፡ በዚህ ታላቅ፣ሀቀኛና ጀግና ኢትዮጵያዊ የጎንደር ህዝብ የሞራል ድቀት ለማምጣት ግን እንዲህ በብስጭቱ፣ ቁጭቱና ሃዘኑ ይስቁበታል ይሳለቁብታል።

10ኛ. የህክምና አገልግሎት በአብዛኛው የኢትዮጵያ አካባቢ ከዛሬ 24 አመት ሲነጻጸር በተሻለ ደረጃ እንደሚገኝ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያስበው እውነት ይመስለኛል። የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ግን የህክምና አገልግሎት መዝጋት የህዝቡ ማለቂያ መሳሪያ ሆኖ ነው ያገለገለው፤ይህን መሰረታዊ ሰብ አዊ ሙብቱ ላለፉት 24 አመታት በትግራይ አስተዳደር እርምህ ይሁን ተብሏል።

ዛሬ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በአለም ተረት በሆኑ በሽታዎች እንደከፍኝና ኮሌራ በየግዜው ህይውቱን ሲቀጥፉት ማየት የተለመደ ነው። በእነዚህና ሌላ ዉሃ ወለድ ሽታዎች በህዝቡ ውስጥ በወረርሺኝ መልኩ እየተነሱ የብዙ ህጻናትና አዋቂዎች ህይወት የሚቀጠፍበት አሳፋሪ ሁናቴ ነው ያለው።

የወልቃይት ጠገዴ እናቶች እጅግ በጣም በከፍተኛ ሁኔታ በወሊድ ምክን ያት ከንህጻናቸው ጋር ይሞታሉ። ለ10,000 የትግራይ ሰፋሪዎች ሆስፒታል ተሰርቶላቸው አንቡላንስ ሲመደብላቸው ተወላጅ እናቶች ግን ህክምና ባለማኖሩ እንዲሁም መንገድ ባለ መኖሩ ምክንያት በመንገድ በቃሬዛ ሳሉ ህይወታቸው ያልፋል። ይህ በትግራይ አስተዳደር በደምብ የሚታውቅ ግን ሆን ተብሎ የተደረገ ነው። እንዲሁም የኛን ቤቶች ንብረቶች በሙሉ እየወረሱ ካስወጡን ብኋላ በአሁኑ ስአት 99.9% እነርሱ በተቆጣጠሯት ሁመራ ከተማ የቆየ ሆስፒታል ቢገኝም ህዝቡ በቀላሉ ሄዶ የሚታከምበት ሁኔታ አይደለም ያለው። ከዛ ገብተህ ለመታከም ብዙ ውጣ ውረድ አለበት እናም ለሰፊው ወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ግን ሆስፒታል ይቅርና አገልግሎቱን የሚወጣ የተሻለ ጤና ጣብያና ኬላ እንኳን የለውም። በእነዚህ የማይረቡ የሬሳ መጋዘን የሆኑ የጤና ድርጅቶች የሚገኙ የህክምና ባለሙያ ነን ተብዬ ሰራትትኖች እጃቸው የሚፈቱት በህዝቡ ስለሆነ

የጠናበት ሰው ሲመጣባቸው ታዲያ ምን እናድርግህ አክሱም ወይ መቀሌ ሄደህ ታከም ይሉታል። እሺ በቃ እድሌን ልሞክር የሪፈር ወረቀት ወደ ጎንደር ጻፉልኝ ስንላቸው ‘አይ የሪፈር ወረቀት የምንጽፈው በትግራይ ወደሚገኙ ሆስፒታሎች የምትሄዱ ከሆነ ነው እንጂ ወደ ጎንደር የሪፈር ወረቀት አንጽፍም ይላሉ የራሳቸው ሰው በጠና ሲታመም ግን በአንቡላንስ ወደ ጎንደር ሪፈር አሲዘው ይወስዱታል። እኔ እንኳን በግሌ ቤተሰብ ታማብኝ ህመሟ ሲጠናባት ‘ለምን ወደ ጎንደር ሪፈር አይጻላትም’ ብዬ የጠየኳት ባለሙያ ‘ህኑ አይፈቅደልንም’ ነበር ያለችኝ። ‘እንዴት ማለት’ ስላት ‘በቃ አሰራሩ እንደዛ ስለሆነ’ አለችኝና በስጨት ብላ ‘ከፈልክ ለመንግስት መጠየቅ ትችላለህ’ ነበር ያለችኝ።ሰውኮ በጭንቀት ውስጥ ሆኖ ወደ ጎንደር ሪፈር ጻፉልኝ ብሎ ደጅ የሚጠናቸው ጎንደር ሆስፒታል ቅርብ ስለሆነ ነው እንጂ ሆስፒታሉ ህዝቡን በነጻ ስለሚያክም አይደለም።

በነገራችን ላይ እንዲህ የሚያናግሩት የጤና ‘ብሩካኖቹ’ ናቸው፤ አለዚያማ ሰው ኪሱ እስቲያልቅ ድረስ ወይንም ተስፋ ቆርጦ ሞቱን እስቲጠባበቅ ወይንም ደግሞ እስቲሞት ድረስ ‘ይሻልሃል’ እየተባሉ ስንቶቹ ወደ መቃብር እንደወረዱ የፈጠራቸው አምላክ ያወቃል ህዝቡም አይረሳቸውም እስከሞቼውም ድረስ። እየሳቁ መግደል ይሉሃል ይሔን አይነቱን ነው።

ብር ያለው ተሎ ጎንደር ሄዶ ይታከማል፤ የሌለው ደግሞ ሞቱን ይጠባበቃል። የትግራይ ሰፋሪዎቹስ ብትሉኝ የወልቃይት ጠገዴ በሚከፍለው ግብር ሁሉም ልጆቻቸውን ጨምሮ በነጻ ነው የሚታከሙት። እናማ የወልቃይት ጠገዴ በሽተኛ ግን ወገን ያለው ከሆነ ይህን ችግር ስለሚያውቅ ብር አዋጥቶ ወደ ጎንደር ወስዶ ሲያሳክም በብዛት ተዳከመው ስለሚደርሱ ወገኖቹ ሬሳ ወይንም ወደ ሬሳነት የቀረበ በሽተኛን ይዘው ይመለሳሉ። እና ህዝቡ ጎንደር ሄዶ መታከም ማለት ሬሳ ሆኖ ከመመለስ ጋር ስላገናኘው በሽተኛው ስቃይ በዝቶበት ወደ ጎንደር ሊሄድ ነው ከተባለ የብሽተኛው ዘመዳሞችና ጎረቤታሞች በእንባ ተራጭተው ነው የሚሸኙት። የሚገርመው ጉዳይ ታድያ እነኝህ የጤና ባለሙያ ነን ባዮች የትግራይ ነጻ አውጭ ቡድን አባሎች ታድያ ልታምኑት ከምትችሉት በላይ ሃብታም ናቸው። ለምን ብትሉ ስራ ቦታቸው ሳይገኙ

በአቋቋሙት የግል ክሊኒካቸው ድሃውና የጨነቀው የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ወደ የመቃብር መጋዝን ክሊኒካቸው ስለሚጎርፍላቸው የጎንደር ሃኪሞች ከሚያስከፍሉት በላይ እያስከፈሉ አዎ በጣም ሃብታም ናቸው።

እነዚህ የጤና ባለሙያ ነን ባዮች እጅግ ስርዓተ ቢስ ናቸው። ለምሳሌ እንኳን ለመጥቀስ ያህል በወልቃይት ውስጥ በአዲረመጥ የሆነውን አሳዛኝ ክስተት ልንገራችሁ። ወላጅ አባት ዲያቆን ልጃቸውን ሊያገባ ስለነበር የዲያይቆኑ አባት ከዲያይቆኑ ልጃቸው የልጅቱ አባትም እንዲሁ ለጃቸውን ይዘው ለሁለቱ ኤች አይ ቪ ምርመራ እንዲደርግላቸው ለልጅቱ ደግሞ ድንግልናዋ እንዲረጋገጥ ወደ ጤና ጣብያው ይመጣሉ። የደም ምርመራ እንዲደረግላቸው ደም ከተወሰደ ብኋላ የልጅቱ ድንግልና ምርመራ የሚያደርገው የጤና ባለሙያ ልጅቱን ደፍሮ በመስኮት ዘሎ አምልጦ ሁመራ በማደር ከዛ ወደ ትግራይ ሄዷል። የልጅቱ ቤተሰብ ሃኪሙ በመዘግየቱ ተጨንቀው ለሌላ ሴት ሃኪም ነግረው ሃኪሟ ስታንኳኳ የሚከፍትላት ስላጣች በመስኮት በኩል ስትሄድ ሃኪሙ የለም ልጅቱ ግን መመርመሪያው ላይ ተጋድማ ታያታለች። ከዛ ሁለት ሃኪሞች በመስኮት ገብተው ልጅቱን ሲያናግሯት ሃኪሙ እንደደፈራትና ወጥቶ ሲያመልጥ ግን ራሷን ስታ እንደነበርና እንዳልሰማች ተናገረች። ቀስም የሚሰብር ታሪክ በልጅቱና በሁለቱ ቤተሰብ እንዲህም በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ተደረገ። ሌላም በጣም ብዙ ተመሳሳይ ችግር አለ።የትግራይ ህዝብ ሃይማኖተኛ ህዝብ እንደሆነ ነበር የምናውቀው ነገር ግን እኛ ጋር የሚመጡት ልጆቻቸው እጅግ በጣም አሳፋሪ ጅቦች ናቸው። እንዲህ ያደረገው ሃኪም በትግራይ ውስጥ የፖለቲካ አመራር ሆኖ እስከቅርብ ግዜ በደቡብ ዞን እንደነበር ሰምተናል፤ እኛ ግን የተባለው ቦታ ሄደን ልናገኘው ግን አልቻልንም።

የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በዚህ የጤና አገልግሎት ሰጭ ድርጅት እጦት ምክንያት የጎንደር ሃኪሞችን እንደነ ዶክተር ፍስሃ ያሉትን የተካኑ የበረሃ በሽታ ሃኪሞች እንዳደርጓቸው እነዚህ ሃኪሞች የሚያውቁ ይመስለኛል። ምንም እንኳን የህዝቡን ችግር ተረድተው ካላቸው በሽተኛ ብዛት የተነሳ በደምብ ባያከሙትም።

11ኛ. ታሪክ ነጋሪ ታላላቅ አዛውንት አባቶችንና እናቶችን በህይወት እንዳይኖሩ ገና ከጧቱ ብዙ አዛውንት አባዎራዎችና እማዎራዎች ታፍነው ተወስደው ይሔው እስከዛሬ ድረስ መቃብራቸው እንኳን የት እንዳለ አልታወቀም። በአንድ ቀን እንኳን 43 አዛውንት ነበር ወስደው ያጠፏቸው። ከ43 አዛውንት መጥፋት ብኋላም በፊትም ታሪክ የሚያውቁ የሱዳንን ታሪክ እንኳን ሳይቀር የሚተርኩ ሙስሊምና ክርስቲያን አዛውንቶች እየለቀሙ ደብዛቸውን ነው ያጠፏቸው። በህይወት እስከቅርብ ድረስ የነብሩትን ታሪክ አዋቂዎችንም "መስፍን ነበርክ፤ አባት ህ መስፍን ነበረ"፤"ነፍጠኛ ነበርክ"፤ "የነፍጠኛ ሚስት ነሽ" ፤ "የነፍጠኛ አባት ነህ" እያሉ በዚህች ምድር በሰቀቀን እንዲኖሩ በማድረግ ፈጠሪያቸውን አሟሟታቸውን እንዲያሳምርላቸውና የህዝቡን ስቃይ እንዲያይና በቃ እንዲል በጸሎት በማሳሰብ ነው ያለፉት። ወያኔዎች እንዲህ የሚያደርጉት ታድያ እሊህ አዛውንት በደል ኖሯቸው ሳይሆን አካባቢውን ትግሬያዊ ለማድረግ የሚያቀልላቸው ስለመሰላቸው ነው። በነገራችን ላይ እንዚህ የትግራይ ተወላጆች ሃይማኖት አላቸው፤ በፈጣሪ ያምናሉ ለማለት ለወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በጣም ይከብደዋል።

12ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ባለፉት 25 አመታት ባህሉን፣ዘፈኑን፣ ቋንቋውንና የአነጋገር ዘዬውን በግድ እንዲተው ተደርጎ በትግራይ ባህልና ቋንቋ እንዲተካው በከፈተኛ ዛቻና ስልታዊ አሰራር ተዘምቶበት ቆይቷል። ህዝቡ በትግራይ ትግሬኛ እንዲጽፍና እንዲናገር ካልሆነ ግን ምንም አይነት የመንግስት አገልግሎት እንዳያገኝ፣ ልጆቹንም እንዳያስተምርና ብሎም ከተወለደባት ወልቃይት ጠገዴ ለቆ እንዲጠፋ ተገዷል፤ እንዲወጣም መመሪያ ሲሰጠው ኖሯል። የወልቃይት ጠገዴ ልጆችም በትምህርት ቤት በግድ በትግሬኛ እንዲማሩ ተደርጓል። ስንቶቹ የአካባቢው ተወላጅ ተማሪዎች የትግሬኛ ትምህርት እንደወደቁ ትምህርት ቤት ይቁጠራቸው። አዎ አስተማሪዎቻቸው ይቁተሩዋቸው እንዳልል አስተማሪዎቹም ያው ነጻ አውጪ ታጋዮች ናቸው። በነገራችን ላይ በ25 አመት ውስጥ በወልቃይት ጠገዴ ከተመደቡት አስተማሪዎች አንድ ሴትና 3 ወንዶች አስተማሪዎች ጥሩ ሰዎች ነበሩ፤ ሃይማኖተኛም ነበሩ። ለእነዚህ ጥሩ አስተማሪዎች ጓደኞቻቸውና አመራሩ በጣም ያገሉዋቸው ነበር ምንም እንኳን በመጨረሻ የጽዋ ተራቸው ከወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ጋር ብ አመሆናቸው ብቻ ለተለያየ አይነት ስቃይ ሰላባ ቢሆኑም እግዚአብሔር

ውለታቸውን እንደሚካፍላቸው ግን እኔ በግሌ አምናለው። ከእነዚህ 4 አስተማሪዎች በተቀራኑ ደግሞ ስራን የሚሰሩ በዱላቸውም ተማሪዎችም የገደሉ አሉ፤ ይሔው ሁሉን ነገር ለእግዚአብሔር ሰጥተን ልጆቻችንን በዱላ መተው ከገደሉ፣ ከደፈሩ፣ አላግባብም ከትምህርት እንዲያቋርጡ ካደረጉ አስተማሪዎች ጋር እየኖርን ነው። ከዚህ ከወልቃይት ባህልና ዘፈን በተያያዘ ምልኩ ምንም አይነት የአማርኛ ዘፈን እንዲሰማና አዝማሪ እንዲታይ አይፈቀድለትም። ይልቁንስ አሸንዳን ሴቶቹ በጥቅማ ጥቅም አንታለልም አሸንዳ አንልም ቢሏቸው በግድ እንዲወጡ በማይክሮፎን እየለፈፉ በማስፈራራት ቅጣት እንዳለ ጆሯችን ያደነቁራሉ። ለአሸንዳና ጥጋቡ የእነርሱ ልጆች ይበቁ ነበር፤ እኛም ተሸማቀን  በየቤታችን ሆነን ቀን እስቲወጣልን ድረስ "እህ፣እህህ"  እያልን መከታተሉን ባላቆምን ነበር። ተመልከቱ ወገኖቼ እንዴት በቁም እስር እንዳለን። የኛን ውቡ አማርኛ ባህላችን እየቀበሩ የእነርሱን በግድ ህይወት እንዲኖረው ይጥራሉ። ድርጊታቸው አስቂኝ የሚያደርገው ደግሞ የዘንድሮ  አሸንዳ የሚሉበት ልብሳቸው ወልቃይት ብለው የሰየሙበት ሁኔታ ነበር።  አሸንዳ የተከበረ ቤተ ክርስቲያናዊ ትርጉም ያለው በውድ የአገውና የራያ ህዝብ ተግባራዊነቱ ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም በወያኔ ዘመን እኛ ስናውቀው አሸንዳ ማለት የትግራይ ህዝብ ሃይማኖታዊ እሴቱ ሳይኖረው በባህላዊ ይዘቱ  የትግራይን ህዝብ ባህል ለማስፋፋት የሚጠቅም ፖለቲካዊ የባህል ትግብረአ እንደሆነ ነው። ስለዚህ የአሸንዳን የባህል ዘመቻ የምንቃመውም ለዚህ ነው። አ ሸንዳ ማለት የወልቃይት ጠገዴ ባህልና ለመግደል የሚያገለግል የወራሪዎች ባህል ስለሆነ በኛ መሃል በጥብቅ እናወግዘዋለን። የአማራን ባህልና አኗኗራችን አየጠፋ ስልምን ብለን ነው የአሸንዳን ባህል ቀምበር የምንሸከመው? በነገራችን ላይ በዚህ አንድ አመት የጀመሩት ሌላው አሳዛኙ ድራማ ደግሞ በሰርጋችና በማንኛውም ይደስታችንም የሃዘናችንም ግዜ የምናሳየው ባህላዊው የአማርኛ ዘፈንና ለቅሶ ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ በትግርኛ አድርጉት እያሉን ይገኛሉ።  "ሰርጉን በአማርኛ የደገሰ ማን ነው" በማለት ይሔን ባደረጉ አንዳንድ ተወላጆች የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ ልዩ ልዩ ግፍና ስቃይ መስራት ጀምረዋል። ተስፋፊዎቹ የዘራችን ማጥፋት (Genocide and Ethnic Cleansing) ብቻ ሳይሆን  የማንነታችን መገለጫ በሆነው ባህላችን ላይ የባህል ዘመቻ (Cultural 'Genocide' and

Extinction) እየፈጸሙብን እንገኛለን። በዚህ አልበቃ ብሏቸው የድፍረታቸው ድፍረት ኑ በግ ውጡ ለውቢቷ ታላቂቱ ትግራይ መወድስ አቅርቡ ይሉናል። አይ ግዜ እንድግዜ ያለ ድል አድራጊ ጀግና በአለም ውስጥ ማን ይኖር ይሆን። አማራነት ወንጀል ሆኖ እንዴት እንደሚያሰቃዩን ተመልከቱ።

13ኛ. ሌላው አሳዛኙ ድርጊት ደግሞ የወልቃይት ጠገዴ የአካባቢ ስሞች በትግራይ ከተሞች ስም፣ በትግራይ የአካባቢ ስሞችና ጀግኖቻችን ብለው የሚጠሩዋቸው ሰዎች ስም እንዲጠሩ የተደረገበት የክልሉ የአዋጅ ድራማ ነው። አንድ ምሳሌ ለመስጠት ያህል እንኳን ድሮ "እንዳይቀዳሽ" እየተባለ የሚጠራው አሁን "ፍረወይኒ" ብለው አጋሜ በሚገኘው ከተማቸው ስም ጠርተውታል። በወልቃይት ጠገዴ የሚገኙት የወንዞቹ፣ የተራሮቹ ፣የበርኻዎቹ፣ የትምህርት ቤቶቹ፣ የሸንተረሮቹና የከተማቹ ስሞች አጋዚ ፍሬ ስዋት ስብሓት አዲአህፈሮም ምናምን እየተባለ አዲስ ስም ተሰጥቷቸዋል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ በሌላ ጽሑፍ እመለስበታለሁ።

የአካባቢው ተወላጅ ከዚህ ከአዲስ ከተሰጣቸው ስም ውጭ አካባቢውን በድሮ ስማቸው ሲጠራ ቢሰማ "<u>ትዕቢተኛ አምሓራይ</u>" እና "<u>ወዲ አድጊ</u>" በማለት የሚጠብቀው የመልስ ምት ቅጣት አንድም ማታን ጨለማን ተገን አድርገው ይገድሉታል አለዚያ ደግሞ በፖሊስ የስድብና ማስጠንቀቂያ ወርጅብኝ ተሰጥቶት ከዚያ ብኋላ ምንም አይነት የመንግስት መስሪያ ቤት አገልግሎት እንዳያገኝ ተደርጎ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ዘብጥያ እስኪወርድ ድረስ በአይነ-ቁራኛ ክትትል ይደረግለታል። የዚህ ሴራዊ አሰራር ድርጊት በጣም ያማል በቃ እበድ እበድ ይልሃል፤ በጣም ያሳዝናል። ፈጣሪ የያዘላቸው ጥፋት ስላለ ነው እንጂ እንዲህ በማድረግ የሚያጠፉን ከመሰላቸው በፍጹም የሚታሰብ አይደለም ይልቁንስ አብረን እንተላለቃታለን እንጂ። በዚህ በወልቃይት ጠገዴ ስም ሲኖሩ የትግራዩ የስምና የባህል ድባብም እያጣጣሙ አለማቸውን ያያሉ፤ ቆይ ግን አለማሰብ ነው እንጂ እስከመቼ ድረስ እንዲህ ሆኖ ይቀጥላል ብለው አስበው ነው።

14ኛ. የእያንዳንዱ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ የትውልድ ሃረጉና የአያቶቹ ታሪክ ይጽፋሉ፤ ታድያ ይሄን የሚደርጉት የህዝቡን ታሪኩና ቅርሱን ለትውልድ እንዲያስተላልፉለት እንዳይመስላች ሁ። የወልቃይት

ጠገዴ ተወላጆች የሚያስሩበትና የሚያሰቃዩበት ምክን ያት ሲያጡ በአባቱ፣ አባቱ ንጹህ ቢሆን በአያቱ፣ አያቱ ንጹህ ቢሆን በልጆቹ፣ በልጆቹ ንጹህ ቢሆኑ ባሉና በነበሩ አዝማዶቹ ሽፍታ ነበረ፤ መስፍን ነበር፤ ነፍጠኛ ነበር፤ ለትግራይ ህዝብ የነበረው አመልካከት እንዲህ እንዲያ እንደዛ እንደዚህ ወዘተርፈ ነበረ ለማለት ነው እንጂ። የአካባቢው ተወላጅም እንደዛ አልንበረም ወይንም እነርሱ እንደዛ ቢሆኑ እና እኔ ምን አደረኩ ሲል ድሮም አንተ የእነርሱ ዘር ሆነህ ለትግራይ ምን መልካም ነገር ይገኝብሃል፤ እንዴትስ ትግሬ ነኝ ብለህ እንድታምንና ልጆችህን ትግሬኛ እንድታስተምር እንጠብቃለን ይሉና አንዳንዱን በማስፈራራት ይለቁታል፤ ሌላውን ደግሞ ደስ ላላቸው ቀን ዘብጥያ ያወርዱታል። የታሰሩትን ለመጠየቅ የሚሄድ ዘመድ አዝማድና ወዳጅም ሁኔታቸው እየታየ ብዙ ስነልቦናዊ ሰለባ ይደርሰባቸዋል።

ሌላው ታሪኩንና ዝምድናውን የሚያጠኑበት አሳዛኝ ምክን ያት ስነግራች ሁ በጣም በከፍተኛ የልብ ስብራት ሆኜ ነው። ወልቃይት ጠገዴ አንድ ጎጂ ባህል አለ ደምነት የሚባል። ታድያ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ይህን ጎጂ ባህል የሚገራበት ሃይማኖታዊና ባህላዊ መንገድ በተሎ ዕርቅ መፈጸም ነው። ደምነት ውስጥ የገቡ ሰዎች ካሉ ዕርቅ ይፈጸማሉ፤ ከዕርቅ ብኋላ የገዳይ ቤተሰብ ከሟች ቤተሰብ ጋር በትዳር ይተሳሰራሉ ከዛም ደምነቱ ቀርቶ በፍቅር ይተካል ደሙም በቀሉም በዚህ መልኩ እንዲደርቅ ይደረጋል። ይህን ዕርቅ ያፈረሰ ወይንም በልቡ ለማፍረስ ያሰበ ወገን ካህናቱ ውጉዝ ከመአርዮስ ብለው በፍጹም ያወግዙታል። ከዛም ያን የገዳይ ቤተሰብ ሄዶ መግደል ራስን እንደመግደል ስለሚቆጠርና ቤተሰባዊ ፍቅርም ስለሚያሸንፈው ጊጂ ባህሉ ዘላቂ መፍትሔ ያገኛል ማለት ነው።

እናም አረመኔዎቹ ደም የጠማቸው የትግራይ ተወላጆቹ ግን ማን ከማን ቤተሰብ ጋር ያልተከፈለ/ያለተመለሰ ደምነት አለው የሚለውን ለማወቅ የእያንዳንዱ የወልቃይት ጠገዴ አዋቂ ተወላጅ ታሪክ ያጠናሉ። ይህን ካጠኑ ብኋላ በዕርቅ የቆመን ደምነት በተለይ ደግሞ ዕርቅ ያልተፈጸመለትን የደምነት እዳ ወያኔዎቹ አንዳቸውን ቤተሰብ ማጥቃት ሲፈልጉ ግዜ የትግራይ ተወላጆቹ በተለይም ፖሊሶቹ ሄደው የገዳይ ቤተሰብን የሟች ቤተሰብ እንደገደለው በማስመሰል ይግደላሉ። ይሔን ለማስመሰል

በጥይት ከሙቱት ብኋላ ተጠቂው ሰው ለመሞት እያጣጣረ ከሆነ ገዳይህ እኔ ደመኛህ እንትና ነኝ ብለው ድሮ እሱ ወይንም የእሱ ቤተሰብ የገደሉትን ሰው ስም ይነግሩታል ወይንም ደግሞ ቢሞትም ባይሞትም ማን ለምን እንደገደለው ወረቀት ጽፈው መልእክት ጥለው ይሄዳሉ። ከዚህ ይበልጥ ነገሩን በጣም አሳዛኝ የሚያደርገው ደግሞ በግልጽ የህግ አካል ሆነው ምስክር አቁመው የገዳይ የተባለው ቤተሰብን ደግሞ መጥተው ያስራሉ። የተገደለበት ቤተሰብ ደግሞ ውሎ አድሮ መግደሉ አይቀርምና ደግሞ ተመልሰው እነርሱንም እድሜ ይፍታህ ብለው ያስራሉ። በእንደዚህ አይነት አረመኔያዊ ሰውር የሴጣን አሰራራቸው የወልቃይት ጠገዴ ጎጂ ባህሉን እያጠኑ ስንቱን ጀግና ጨረሱት መሰላችሁ። አሁን ግን ህዝቡ በከፊልም ቢሆን ስላወቀባቸው ቢአይንስ ለመግደል አይሯሯጥም ለዕርቁ እንጂ። ተመልከቱ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን እየደረሰብን ያለው ግፍን እልቂት። ይህ ሁሉ ሲሆን ታድያ እኛ ለእነርሱ ክፉ ሆነን ሳይሆን እንዲያውም ሲራቡ የምናበላቸው፣ሲጠሙ የምናጠጣቸው፣ ሲሰደዱ የምናስጠጋቸው፣ ስራ ቢፈልጉ ሰርተው የሚቀየሩብን፣ ሲያጡ የሚጠጉብን እውነተኛ እትዮጵያውያን ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ነበርን። ለምን እንዲህ ይህ ሁሉ ግፍ እንዳደረሱብና እያደረሱብን እንዳለ በጥቂቱ ቢገባንም ለእኛ ግን እንደታላቅ መቅሰፍት ከመቁጠር ውጭ ለታላቂቱ ትግራይ ምስረታ ብለው ይሔን ሁሉ ግፍ በኢትዮጵያውያን ሰው ልጆች ማድረስ ምንም አሳማኝ አልሆነልንም።

15ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ አብሮ መኖርና አብሮ ተካፍሎ መብላት ለቸገረው ሰው መርዳትና የዋህነት ማህበረሰባዊ ባህሉ ነውና በወልቃይት ጠገዴ መጥተው ያለፈላቸው የትግራይ ተወላጆች ግን እውነትነትና መሰረት በሌለው በጥቅማጥቅም ተደልለው ህዝቡን በውሸት መረጃነትና ስለላ እያሰቃዩት ይገኛሉ። የእነዚህ ህዝቦች ባህሪ ምን አይነት በጣም እጅግ በጣም ለመረዳት ከባድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለእኛ አስገራሚ የህይወት እንቆቁልሽ ናቸው። ለህዝቡ ወዳጅ መስለው በውሸት መረጃ ስንቱን ንጹህ ተወላጅ እንዳስጨረሱት እነርሱ መቁጠር የሚከብዳቸው ይመስለኛል፤ በእርግጥ ለእነርሱ ቢከብድም ቤተሰቦቻቸው አንረሳቸውም ከዚህም አለፍ ሲል ፈጣሪያቸው ያውቃቸዋልና ደማቸው በፊቱ እየጮኸ ነው ግፋቸውን ትተው ለህዝቡ መበደሉን ካላቆሙ እርሱም መፍረዱ አይቀርም። ለምሳሌ ያክልም፡-

በዳንሻ ከተማ የሚገኝ የትላንትናው የስአትና ሬድዮ ጠጋኝ የዛሬው ኢንቨስተርና ደህንነት ወዲ ሃጎስ፤ የትላንትናው ባለፉል ቤት የዛሬው ኢንቨስተርና ቀንደኛ ደህንነት ወዲ ሃበሽ እንዲሁም በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ እሚሃይ እናቱና ወንድሙን እየተረዱ በዚህ መልኩ አድጎ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የሂሳብ ባለሙያው ህዝቡ ያስተማረው የዛሬው ዋና ደህንነትና ነጋዴ ገብረግዚአብሔር ነጋሽ የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ ጉዳይ በንጹሃን የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ግፍ የፈጸሙትን የጡት ነካሾችን አሳዛኝ ታሪክ የሚያጋልጥ ለእናንተው ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በቀጣይ በሰፊው ይዘን እንመለሳለን።

16ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ገጽታን አጥቁረው በወልቃይት ጠገዴ የማይኖሩና የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ሁሉ ያለ አንዳች ምህረት እንዲያሰቃዩ በማሰብ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ጠላታቸው እንደሆነና ትግል ውስጥ እንዳሉ ለህዝባቸው ይሰብካሉ። እኔ እንኳን ሽፍታ ብለው የገደሏቸውን የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆችን በአንድ መኪና ሁለት ሶስት መኪና አስረው ሲጎትቱ አይቼያለሁ፤ በመሃል ከተማ አምጥተው ከጣሏቸው ብኋላ ጭንቅላታቸውን በጥይት ሲያፈራርሱት በአይኔ አይቻለሁ። እስከቅርብ ግዜ ድረስም ሳስታውሰው እጨናነቅ ነበር፤ አሁንም ይሔን ስጽፍ እንባዬን እየረጨሁ ነው። ማለት አይሰስ የሚባለውስ ከዚህ ውጭ ምን አደረገና። ብዙ ታሳሪዎች ናቸው ያሏቸውን የወልቃይት ጠገዴ ሰዎች በሩቅ ጫካ ወስደው ካሰሩዋቸው ብኋላ ጅብ እንዲበላቸው የተደረጉም ነበሩ በ1985/6 አ/ም። እዚህ ላይ ሳልጠቅስ ማለፍ የማላልፈው የአንድ ዘመዴ አሟሟት ልንገራቹህ። ሰውየው የ63 አመት ሃብታም አባወራ ነው። እና ጫካ ወስደው አሰሩት እኛም ጠፍቶ ስንፈልግ ስንፈልግ ካንድ የደረቀ እንጨት የኋሊት ታስሮ ትክሻው ላይ ሆኖ አንድ ትልቅ አሞራ ያንገቱን ስጋ እየዘነጠለው ነው ያገኘነው። ሌላም አንድ በጣም ሃብታም የነበር ዘመዳችንም ጎረቤታችንም ከብቶቹ ለማየት ወደበረሃ ሄዶ አራት እረኞቹ ጋር ምሳ ስአት ቁጭ ብለው ሳለ መጥተው ወሰዱት። ብኋላ አመሻሽ ላይ ግን ሶስቱን እረኞች ከገደሉ ብኋላ አንዱ ያመልጣቸዋል። ለሰዉየውም ካንገቱ በታች ጉድጓድ ቆፍረው ከቀበሩት ብኋላ ከ700 በላይ የሆኑት የገዛ ራሱ ከብቶች በራሱ ላይ መልሰው መላልሰው ነዱበት። ከብቶች እየተጨነቁ 'እምቧ እምቧ እምቧ' እያሉ ሲጨነቁና እንስሳዊ ለቆሷቸውን እያሰሙ ሲበረግጉ ሊያመልጡ ያሉትን ከብቶችም ጭምር በጥይት

ይጥሏቸው ነበር። የጌታቸው ጭንቅላት እንደሊጥ እየፈረጠ እንደማስቲካ ሸሆናቸው ላይ ተለጠፈ። የተቀሩትንም ገሚሶቹ ወደ ሱዳን ገሚዞቹ ደግሞ ወደ ትግራይ ነዷቸው። የሁለቱም ሰዎች ስም ያልጠቀስኩበት ዋናው ምክኛት ለቤተሰቡ ደህንነት ብዬ ነው። እንግዲህ እሊህ የትግራይ ሰዎች ከእንሰሳ በታች የሆነ ልቦና ነው ያላቸው አረመኔ ናቸው እምለው ለዚህ ነው። እንግዲህ እኒህ ሰዎች ናቸው እኛን ትግሬ ናቸውና ከእኛ ጋር ይሁኑ የሚሉን!!! በየትኛው የሞራል ብቃታቸው ነው ይሄን ሊሉ የቻሉት? እጅግ በጣም የሚገርም ነገር እኮ ነው። የፌደረሽን ምክር ቤት ተብየው በወያኔ ሳንባ የሚተነፍስ እጅግ አሳዛኝ ምክር ቤት ቢሆንም አሁንም ቢሆን አልረፈደም። ኦ አምላካችን ምነው ምን በደልነህ ብለን እኛስ አናማርም ግን እባክህን የኢትዮጵያ እልቂት ሳታሳየን ወደ ወገኖቻችንም ጨምረን፤ከነዚህ አላቀን። በግድ ዘመዶቻችን በግድ ስጋችን ናችሁ ይባላል እንዴ፤ የሚዘረፍ ባለበት ሁሉ በግድ እንዲ አይንን በጨው አጥቦ በግድ ትግሬ ናችሁ ይባላል እንዴ፤ በቃ እኛ አማሮች ነን እንዴ አይገባችሁም እንዴ። እኛ ትግሬነት ከፋት ኖሮበት ሳይሆን እኛ ትግሬ ነን የማንለው ትግሬ ስላልሆን ነው። እስቲ አንዴ ቆም ብላችሁ አስቡብት። እኛ ለእናንተ በግድ አማራ ሁኑ ብንላችሁ ይስማማችኋል እንዴ። በቃ ተውን እኛ አማራ ሆነን ነው የተፈጠርነው፤ በምን ቋንቋ እናስረዳችሁ። አዲስ በአለም የሌለ ለናንተ ሊገባችሁ የሚችል ቋንቋ ካለ ደግሞ ንገሩንና እናስረዳችሁ። ይሄም የምናደርገው ለህዝቡና ለመጪው ትውልድ ሰላም ስንል ነው። ተውን በቃ ጥጋባችሁና እብሪታችሁ መጠን ይኑረው!!! እንደመዥገር በግድ ትጣበቁናላችሁ እንዴ። የሰውም መዥገር አለ እንዴ?

ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና እንደዚህ ሁሉ እያደረጉ ለህዝባቸው ጥላቻን ቢያስተምሩዋቸውም በተለያየ ስራ ወይንም ዘመዶቻቸውን ጥየቃ በለው የመጡና ብኋላም ኗሪ የሆኑ አንዳንድ ደግ ኢትዮጵያውያን የትግራይ ተወላጆች ከህዝቡ ኖረው ህዝቡን የተረዱ ሰዎች አይደለም ደሞዝ ተጨምሮልን በነጻ ለዚህ ህዝብ ብናገለግልስ፤ ምርጥ ህዝብ አይደል እንዴ፤ አገርቤት የሚወራውኮ እንደዛ አይደለም ተቃራኒው ነው የሚደመጡ አሉ። ታድያ ከእነዚህ ደግ ኢትዮጵያውያን የትግራይ ተወላጆች እንዲህ ሆነው ቃላቸውን በዚሁ ንግግራቸው የሚያጸኑ በጣም ላጭር ግዜ ብቻ ነው፤ ለምን ቢሉ ጵዋቸው ከወልቃይት

ጠገዴ ህዝብ ጋር እንዳይሆን ፖለቲካዊ ዛቻ ስለሚደርስባቸው ሳይወዱ በግዳቸው ስልፋቸው ከማይመስሏቸው ከአረመኔዎቹ ጋር ይሆንና ህዝቡን እያዘኑ ሲበድሉ ይታያሉ። እነዚህ እንኳን በከፊል ያሳዝኑናል ቢያንስ የህሊናቸው እስርኞች ናቸውና። ሰልፋቸው ከእነርሱ ጋር ሆነው በተለያየ መልኩ ቢበድሉንም እንኳን የተሴረውን የሴጣን ምክር ለተጠቂው ህዝብ አንዳንዴ ሹክ ብለው የሚያስመልጡ ደግነታቸው ያልተለያቸው ጥሩ ኢትዮጵያዊ ስለሆኑ ፈጣሪ ዋጋቸው እንደሚከፍላቸው አንጠራጠርም። በወልቃይት ጠገዴ ምድር ቸር የሆነ የትግራይ ተወላጅ ማግኘት ለእኛ በጣም ብርቅ የሆነን ሰዎች ነን።

17ኛ. ሌላው የወያኔዎቹና ሰፋሪ ትግሬዎቹ አሳዛኝም አብሳጭም ባህሪ ደግሞ ማንነታቸውንና በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ብሎም በኢትዮጵያው ያላቸውን አመለካከት የሚያሳየውን ነው። እነዚህ አረመኔዎች የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ጠላት ብቻ ሳይሆኑ የተፈጥሮም ጠላት ናቸው።

የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ለዘመናት እንደ አካሉ፣ እንደአይን ብሌኑና ውርሱ አድርጎ ጠብቆት የኖረውን ተፈጥሯዊ ሃብቶቹ ለምሳሌ እንደወርቅ፣ እጣን፣ ጥንታዊ ደኖችና እደሜ ጠገብ እጽዋቶች ከህዝቡ እጅ ተነጥቆ የተሰጡት ለሰፋሪዎቹ ናቸው። በእርግጥ እጣን ለተወላጁ ቢሰጥም አሁን ደግሞ ለሰፋሪዎቹ ለመስጠት እቅድ አውጥ ተው እየተንቀሳቀሱ ነው። ለምለሚቷ ጎጃ እያሉ የሚቋምጣትን ወልቃይት ጠገዴ ከአረንጓደው ልማት ልፈፋና የዝርፊያው የመለስ ፓርክ መላ በተቃረነ ሁኔታ የረዥም እድሜ ባለጠጋ የነበሩትን ግ ርማ ሞገስ የተላበሱትን እጅግ በጣም ጥንታዊና አግርኛ እጽዋቶቿ በመቁረጥና በመጨፍጨፍ የግብርናው ባለሙያ እንኳን ሳይቀር ከሙያቸው በተቃረነ ሁኔታ በትግራይ ልዩ ልዩ ከተሞችና በአዲስ አበባ የሃብታም የትግራይ ሰዎች ልዩ ልዩ ቤቶች መስሪያ ሆነዋል። ቀሪውም በየግዜው በሙቶዎች በሚቆጠሩ መኪኖች እያጓጓዙ በአዲግራት፣ በአድዋ፣ በአክሱም፣ በመቀሌና ሽሬ ይሸነሽኑታል ይቸበችቡታል። በዚህ ሃብታም ሆነው ወደ ከፍተኛ ኢንቨስተርነት የተሸጋገሩ የትግራይ ተወላጆች በጣም ብዙ ናቸው ቢሆንም ዝርዝራቸው ያለን የ193 ዘራፊዎች ግን ወንጀላቸው ከነሙሉ ስማቸውና አድራሻቸው ታሪክ እንደከተበው ሊያውቁት ይገባል።

ከእነዚህ ሰዎች በላይ ሰፋሪዎቹ በየቀኑ ከስራቸው ሳይቀር መዘው እያወጡ ስራቸው የሚቆፍሩ የአካባቢው ግርማ ሞገስ የነበሩ ደኖች ምስክር ይሁኑባቸው፤ በእውነት እንዚህ ሰዎች አገር አጥፊ ናቸው።ይህን ያልኩበት አስተሳሰብ ትግራይ ውስጥ ችግኝ ሁሌ ከመትከል ተቆጥበው አያቁም ቢሆንም አንድም ተራራ እንኳን በተከሉት እጽ መሸፈን አልቻሉም፤ እንዲህ ሲሆንባቸው በቃ ዝም ብለን እንተወውና የሚሆነውን እኝ ብለው ይሔው ይጠብቁታል አንድም እጽ ግን ሲወጣ አላየንም በቴሌቭዥናቸው ትግራይ ለመለመች ብለው እንደሚያሳዩን ከሆነ። እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ታድያ ለምንድን ነው በወልቃይት ጠገዴ የሚገኘውን አዝማናትን ያሻገረን ደን የሚጨፈጭፉት። በእውነት ከንቱ ምቀኞ ናቸው፤ የህዝቡን ትግሬ ያለመሆን ሁኔታ ስለተረዱ ትግራይ እንዳልሆነ ስለሚያውቁ ነገ ጥለነው ለምንሄድ ብለው አማራውን ህዝብ የተበቀሉ መስሏቸው በተፈጥሮ ላይ ግፍ የሚፈጽሙ ዲንጋይነታቸውን የሚያሳይ የአረመኔ ግብራቸውን ነው የሚነግረን።

ለነገሩማ እንደነርሱ ነፍስና ስጋ ያለውን የሰው ህይወት ያላሳዘናቸው ስለተፈጥሮ እንዴት ሊያስቡና ሊያዝኑ ይችላሉ። ፈጣሪ አይፈቅደላቸውም እንጂ እንደየበርኻው እቅዳቸው እኮ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ሙሉ ለሙሉ ጨርሰው አጥፍተው ወልቃይት ጠገዴ የትግራይ ቢአይደርጉ እንኳን ደኑ አሁንም ይጠቅማቸው ነበር ባይ ነኝ። ግን እነርሱ አይምሯቸው አርቆ የሚያስበው ለጥፋት እንጂ ለልማት አይደለምና ይሔንን እቅዳቸው የዋልደባ አምላክ እንደማይፈቅድላቸው ስለሚያውቁ የወልቃይት ጠገዴ ተፈጥሮ ይሔው እንዲሁ በቀላሉ ሲያጠፉት ነበር አሁንም ያጠፋሉ። ከታች እስከላይ ያው እነርሱ ስለሆኑ ህዝቡን እንኳን የተፈጥሮ ጸጋ ስጦታውን ህይወቱን እንኳን መታደግ ስላላቻለ ወልቃይት ጠገዴ ከዳኗን አውልቀው በባዶ ገላዋ ራቁቷን አቅሚዋታል። ለነገሩ ምን ይገርማል ኢትዮጵያን የምታህል ቅድስት ሃገርንስ ለአለም ልጆቿን ቸብቸበው እራቁቷን አቁመው ለዝሙት አየቸበቸቧት አይደል እንዴ። ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን ሆይ የነዚህ ግፋቸው ከሰው ልጅ ከቋንቋ በላይ ነው።

18ኛ. እያንዳንዷ የሚፈጽሟት ግፍ፣ የሰብ አዊ ሙብት ጥሰት፣ አፈናና ግድያ አንሰላስለው አቅደው ስለሆነ ህዝቡ እንደጠቀየማቸው ስለሚያውቁ ከፍርሃታቸው የተነሳ ዝም ብለው ብድግ ብለው *“ምንም አታመጡም፤ ገና ስታሰቡት ልክ ትገባላችሁ፤ አሁንኮ ትላንት አይደለም ዛሬ ነው መሸፈቻ ቦታ የለም፤ ኢትዮጵያ እንደሆነች በእጃችን ነች የትም አትገቡም ብትገቡም አታመልጡንም፤ አንድ ነገር ብትሉ እስከነ ልጆቻቹህ እንጨርሳቹኋለን”* ብለው በድፍረት በአደባባይ በየስብሰባው ህዝቡን በስሜት ሆነው ይወርፋሉ ይናገራሉ። ኧረ እናንተየ ሆይ ፈጣሪ ከሰው ልጅ ሲለይ የሰው ልጅ እንዲህ ከንቱ ይሆናልን? እናማ እንዲህ እያሉ ህዝቡን ስሜት ውስጥ እንዲገባና እርምጃ እንዲወስድ ይገፋፋሉ፤ እያንዳንዷን ቀን ያለመረጋጋት ህይወት እንዲኖረው ጠክንረው ሲሰሩ ይታያሉ። ህዝቡ ደግሞ ተንኮላቸውን ስላወቀ የአየር ሁነታው እስቲስተካከል ድረስ በተቻለው መጠን በትዕግስት በአርምሞ ለማሳለፍ ይሞክራል። ግን ዝምታው ደግሞ ብርድ ብርድ እስከሚላቸው ድረስ ሲያንቀጠቅጣቸው ታያላችሁ፤ የፈጣሪ ስራውና ግብሩ እንዴት እጅግ ግሩም ነው። ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ በእርግጠኝነት የምነግራቹህ በወልቃይት ጠገዴ መጥታቹህ ለአንድ ቀን ብትውሉና ብታድሩ በጣም የሚያሰጠላና የሚያምምም ስሜት ይሰማችኋል። ኑና እዩት ብየ እናንተን ዉድ ወገኖቻችን አልረግማችሁም። በነገራችን ላይ የሌላ ብሔር ኢትዮጵያዊ በወልቃይት ጠገዴ ውስጥ እንዲኖር ቀርቶ ለቀናት እንዲገኝ አይፈቀድለትም። ለምን እንደሆነ ለእኛ እ ስካሁን ድረስ ግልጽ የሆነ ነገር የለንም።

19ኛ. በአካባቢው ማለት በወልቃይት ጠገዴ ምንም አይነት ሌላ አካል ለምሳሌ እንደ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ጋዘጠኞች፣ በህዝቡ ሊቋቋሙ የሚችሉ ማህበራት፣ የሌላ ብሔር ያለው ኢትዮጵያዊ እንዲገኝ አይፈቀድም። እነዚህ የጠቀስኳቸው ነገሮች እጅግ በጣም በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው። ሌላው ይቅር በተለያየ ስራ የወጡ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች እንኳን እንዲመለሱ አይፈቀድላቸውም።

እኛ ጋር ብትመጡና ብታስተዉሉት የተወላጁ ድባቡና መንፈሱ ሶሪያ ውስጥ በጦርነት መሃል ያላችሁ ያህል ነው የሚሰማችሁ። በአንጻሩ ደግሞ ትግሬዎቹ አንድን ከተማ መሉ በሙሉ ደምስሶ ድል አድርጎ

የተቆጣጠረን ሰራዊት በሚመስል መንፈስ እዚህና እዚያ በደስታ ሲወራጩ ታዩዋቸዋላች ሁ። በጣም የሚያስገርም ነው፤ ወሬያቸው ሁሉና ደስታቸው የሚመነጨው ከአማራው ህዝብ የህዘን ድባብ ነው እንዴ የሚል ጥያቄ መልሱን አዎ ብላችሁ እንድትሄዱ የሚያደርግ ገራሚና አስጥሊታ ድባብ።

20ኛ. በአጠቃላይ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በፈርዖን አገዛዝ ስር ነው ያለው። ወያኔና ካድሬዎቹ የፈርዖንን አገዛዝ ከዛም በላይ ካለ እነዚህ አረመኔዎችን በሚገባ ይገልጻቸዋል ምንም እንኳን የሚያንሳቸው ቢሆንም። እነዚህ የዘመኑ አዶልፍ ሂትለርና ስታሊን ናቸው። በእርግጥ ከፈርዖን የሚለያቸው አንድ ነገር አለ። አዎ ፈርዖን እስራኤላውያንን ያስጨነቀው በሀገሩ ግብጽ ድረስ ሄደውበት ነው፤ <u>የዘመኑ በጣሊያን ሳንባ የሚተንፍሱት ፈርዖኖች (ወያኔዎች)</u> ግን የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ በአጠቃላይ ደግሞ የኢትዮጵያን ህዝብ እንደፈርዖን የሚያስጨንቁት አገሩ ድረስ መጥተውበት ነው። <u>አዎ የናዚ እልቂት በመላው የአማራ ህዝብ በተለይ ደግሞ በወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በስፋቱ፤ በአይነቱና በውስብስብነቱ በላቀ ሁኔታ በስውር በወያኔ ተፈፅሟል</u>። <u>ጣሊያን ጀምሮት የነበረውን የከፋፍለህ ግዛ የእንግሊዝ ፖሊሲና እልቂት አገር-ብቀሉ ተላላኪው ወያኔ በሰፊው ተግብሮለታል</u>። በዚህም ሎሌነቱን አስመስክሯል፤ አሁን ደግሞ ጌታው ጣሊያን የተከናነበው ውርደኤታን ሽንፈት የመቅመስ ግዴታ አለበት!!! አዎ እኛ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነን ተነስተናል። በዚህ አጋጣሚ የትግራይ ህዝብ እራሱን ከዚህ አጥፊ ቡድን አላቆ ከጎናችን እንዲቆም አጥብቀን እንጠይቃለን። ይሄን ጥሪ የምናቀርበውም የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ለናንተ ለትግራይ ሰዎች በኢትዮጵያዊነቱ ያላደረገላችሁ ውለታ ስለሌለ ቢያንስ ውልታ የመመለስ ባህላዊ ግዴታ ስላለባችሁ ነው። ልጆቻችሁ ያበላሹትን ነገር እናንተ ቢያንስ በፍቅራችሁ አሸሩት ካልሆነ ግን ቁርሾው ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ይሆናል።

21ኛ. ቢሆንም አዎ ቢሆንም ጀግናውና ቆራጡ የወልቃይት ጠገዴ የጎንደር ህዝብ ግን የተደገሰለትን የሞት ጽዋ ለ36 አመታት እንደኢየሱስ ክርስቶስ ሞቱን እየተጎነጨ "ቃሌ አንድ ነው፤ እውነት አይቀየርም" ብሏል። "አሁንም እንዲህ ሆኜ ህያው ሆኜ ኢትዮጵያን እታደጋለሁ" ይላል። ምንም እንኳን በሞት ቀይ

ባሕር መካከል ለማለፍ ለ36 አመታት ወደ ቀይ ባሕር ፊት ለፊት ለመቆም ሲጓዝ ቢቆይም አሁን ከቀይ የሞት ባሕር ተፋጦ ብቻ አልቆመም፤ በፍፁም ጥንካሬና የላቀ መንፈስ ተጋድሎውን በመፈፀም ቀይ የሞት ባሕሩን ፊት ለፊት ሰንጥቆ በመሻገር የመውጫ አፋፍ ላይ ያለውን ጨፌ በእጁ ይዟል!!! የሙሴን በትር ወክለው ደማቸውን ወደ ቀይ ባህር አፍሰው ባህሩን ለሁለት የከፈሉ ውድና ጀግና የአማራ ነገዶች የነፃነት ፋናወጊ ሰማእታት ክብር ይገባቸዋል፤ ነፍሳቸውን ይምርልን ዘንድ ሁሌም ጸሎታችን ነው። <u>ደማቸው ላይደርቅ ከቀይ ባሕሩ ጋር ተዋህዷል ማእበሉንና ወጀቡን ቀጥ አድርጎ ታላቁን ዘንዶ ለሁለት ሰንጥቋል፤ በደም የታወጀ የነፃነት አደራ አለብንና ጉዟችን እስከነፃነት ድረስ ነው</u>!!! አዎ ጠላት እንዳለው <u>"ሞት የተባለው አማራ</u>" ለነፃነት ሲባል "<u>እየገደለ የሚነሳ ነው</u>"እንጂ ገዳይ አይደለም፤ ለጠላቱ ግን በውነት የገዳይም ገዳይ ነው። አሁንም ይሄን ካላመንክ ሂድና ጌቶች ህን ጠይቃቸው፤ ጌቶችህ ግን ምንኛ ከፉዎች ናቸው ይሄን እውነታ ሳይነግሩህ ቀሩሳ!!! <u>የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ባጠቃላይ ደግሞ ጀግናው የአማራውና የኦሮሞ ህዝብ ጠላቴ ሆይ ደስ አይበልህ ይሔው ህያው ነኝ ህያው ሆኜ እየተሻገርኩኝ ነው አለ</u>። ሰልፉ የሁላችን ነውና ኢትዮጵያውያን ሆይ ባንድ ልብ እንነሳ!!! "አዋጅ!""አዋጅ!!""አዋጅ!!!" ኑ ህያው ሆነን እንሻገር ተብላችኋል። አዎ.......ጆሮ ያለው ይስማ፤ ልብ ያለው ልብ ይበል!!!.....ሰማያዊ ያይደለ የሞት ቀይ ባሕሩን በልበ-ሙሉነት ተረግጠን ተሻግረን ወደ ነጻነትና ፍትህ የሞላባት አገር በደስታና በአንድነት ተሰባስበን ኑ በሓሴት እንዘምር!!! <u>ፈርዖን ታሪክ እንደሆነ ናዚ ታሪክ እንደሆነ አዎ ሞሶሎኒ ታሪክ እንደሆነ የነርሱ ቅሪት የሆነው አረመኔው የኢትዮጵያ ህዝብ ነቀርሳ የሆነው ወያኔም ታሪክ ይሆናል</u>። *ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ማሰብ ያለብን ነገር አለ፤ ወያኔን ባንታገል እንኳ መሞታችን አይቀርም። ስለዚህ ታግለንም ሳንታገልም ሞታችን የማይቀር ስለሆነ እንዳባቶቻችን በጅግንነት በ አንድነት ተነስተን ወያኔን ማስወገድ አለብን*። ያለነፃነት ከሚኖር 70 አመት በነፃነት የምትኖር አንድ ደቂቃ ትበልጣለች። ኢትዮጵያ ለዘላለም ከልጆቿ ጋር በሰላም በክብር በአንድነት ፀንታ ትኑር፤ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ፤ አሜን።

ውድ ኢትዮጵያውያን *<u>"የማያልቀው ወያኔያዊ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ስቃይ</u>"* የሚለውው ንጽሑፍ ከ<u>welkait.com</u> ወይንም <u>ecad forum.com</u> ድረ ገጽ እስቲ አንብቡኝ።

በዚህ ጉዳይ *"የማያልቀው ወያኔያዊ የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ስቃይ"* በሚል መጣጥፍ ላይ ከሰፈረው የሚከተለውን ፅሁፍ ላስነብባችሁ። አንድ የወልቃይት አባት የተናገሩት ነው።

እነዚህ ሰፋሪ ነን ባይ ወራሪዎች ለወልቃይት ጠገዴ ህዝብ እጅግ በጣም የመረረና የከረረ ያላቸው ናቸው። በገዛ አገራችን ሁሉን ነገር አሳጡን የቀራችው ያችው ማንነታችን ለመዝረፍም ይሔው አሁንም ያሰቃዩናል፣ ያስሩናል፣ ይገድሉናል፣ ያሳድዱናል፣ ይደበደቡናል ፤ ሴቶቻችንን ይደፍራሉ። እንኳንስ አማራ ሆነን ወደ ፈለግነው መሆን ምርጫው የኛው አይደል እንዴ? ለምንድን ነው የሚያሰቃዩን? አያችሁ ይህ ሁሉ ግፍ የሚደርስብን አማራ በመሆናችን ብቻ ነው፤ ዘር ወንጀል የሆነበት አገር በዚህ መንግስት በኢትዮጵያ ብቻ ነው። አሁን ደግሞ ትግሬ ነን ካላላችሁ ይሔን አገር ለቃችሁ ጥፉ ይሉናል፤ አይ የእግዜሩ ትዕግስት!!! ምን አይነቶቹ የሌባ አይነደረቆች ናቸው? በትዕግስት እንደቆየነው አንልም እንጂ በጂ እሺ ትግሬ ነን ብንል እንኳ በሕይወት እንደማያስኖሩን በደምብ እንረዳለን፤ ወገን ምነው ኢትዮጵያ እንዲህ ስቃይ ሞላባት?

እሊህ አባት ይህ *"አልበቃ ብሏቸው ደግሞ"* ይላሉ *"የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ በግድ ትግሬ ነን በሉ እያሉ በየቤታችን እየዞሩ ያስፈራሩናል፤ ከትግራይ ሰው በመኪኖች ሞልተው እያመጡ ሰላማዊ ሰልፍ አይሉት ጦርነት ያሰልፉብናል፤ ይህ ምን የሚሉት ድንቁርና ነው"* ይላሉ...."*ከእንግዲህስ እንተላለቅ እንደሆን እንጂ በቀረችን አንዷ ተፈጥሯዊ ሃብታችን በማንነታችን እንኳ ከንግዲህ ብኋላ አንደራደርም"* ብለው ማስጠንቀቂያ ያዘለ ሃሳባቸውን ገልፀዋል። ልብ ላለውና ሰላም ለሚፈልግ የትግራይ ህዝብ ትልቅ መልእክት እንደሆነ እናስባለን!!

በመጨረሻም እሊህ አባት *"እግዚአብሔር ስቃዩና ስቅላቱ በቃቹህ ብሎን ከወገኖቻችን ጋር በሰላም የምንኖርበት ግዜ ያምጣልን፤ኢትዮጵያ አገራችንም በሰላም ትኑር"* በማለት የጥልቅ ሃዘናቸውን መርሻ የሆነውን ተስፋቸውን በቃላቸው ገልጠዋል።

*እባክዎ ይህቺን ጠቃሚ ጽሑፍ ለሌሎች ኢትዮጵያውያን እንድትዳረስ በማድረግ የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ ዘር መጥፋት እንዲቆም የማንነት ጥያቄው እንዲመለሰለት ይረዱን ዘንድ በዋልደባው አምላክ በትህትና እንጠይቃለን። ፈጣሪ ውለታዎትን ይከፈል!!!*

ሰላም ሁኑ፤ የዋልድባ አምላክ ቸር ወሬ ያሰማን!!!

የአንበሳው የመይሳው የቴዎድሮስ ዘር ወልቃይት ጠገድቼው ነኝ

ከወልቃይት ጠገዴ በጌምድር ፤አማራ ኢትዮጵያ

16 ነሐሴ 2008 አ/ም